

በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ የወንጌልን ብርሃን ያበራው
ብፁዕ አቡነ ሰላማ ካሣቴ ብርሃን (ፍሬምናጦስ)

# ትንሣኤ



ቅዱስ ጴጥሮስ ስለ ክርስቶስ ፍቅር በሮም አደባባይ የቁልቁሊት የሚሰቀልበትን መስቀል ተሸክሞ

ዋጋው ሃምሳ ሣንቲም ቁጥር 34 ሐምሌ ፲፱፻፸፱ ዓ.ም.

www.ethiopianorthodox.org

"ይህ መጽሔት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፡ ሥርዓትና ዜና ፡ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ጭምር እንዲተረጐሙ ለሥራ ጅንነግ የሚል ስለሆነ "ትንሣኤ" ተብሎ ተሰይሟል ።

አዘጋጅ
ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
ሐዋርያዊ ድርጅት
የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ
በወር አንድ ጊዜ
እየታተመ የሚወጣ ።

የስልክ ቁጥር 116616
የመልእክት ሣ.ቁ. 3137
አዲስ አበባ

## ማሳሰቢያ

በትንሣኤ መጽሔት ቁ. 31 ላይ ስለ ጌታ መግነዝ ወጥቶ የነበረው ጽሑፍ ያልደረሳቸው አንባብያን በድጋሚ ተባዝቶ እንዲደርሳቸው በስልክና በደብዳቤ በብዛት ስለጠየቁን በዚህ እትም አውጥተነዋል ።

## ማውጫ

| አርእስት | ገጽ |
|---|---|
| ደብዳቤዎች | ፩ |
| መልክአ ክርስቶስ | ፪ |
| የጌታ መግነዝ | ፫ |
| ጴጥሮስ በሮም አደባባይ | ፬ |
| ሰላማ ከሣቴ ብርሃን | ፮ |
| ሴቶች በወንጌል መምህርነት | ፲ |
| ቅዱስ ጋብቻ | ፲፪ |
| ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን | ፲፫ |
| ይህን ያውቁ ኖሯልን ? | ፲፬ |
| ምን እንርዳዎ ? | ፲፮ |
| ከሚሠሩ ጋር ዕውቀታችሁን አስተባብሩ | ፲፯ |
| የጨዋታ | ፲፱ |
| የምእመናን ድምፅ | ፳ |
| ወጣቶች | ፳፪ |
| የመጽሐፍ ቅዱስ ጥያቄዎች ውድድር መልስ | ፳፬ |

# ደብዳቤዎች

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

ከሁሉ አስቀድሞ የክርስቶስ ሰላም ይድረሳችሁ ። በገጠር አብያተ ክርስቲያናት አንድ ክርስቲያን ሥጋውና ደሙን ለመቀበል የሚችለው በምንኩስና ወይም በጋብቻ ተወስኖ ነው ይላሉ በከተማ እንደማየውና እንደምሰማው ግን ክርስቲያን የሆነው ሁሉ ሳያገባ ወይም ሳይመነኩስ ተብሎ ሥጋውን ደሙን ከመቀበል አይከለከልም ። ለመሆኑ ለከተማና ለገጠር አብያተ ክርስቲያን የተለያየ ሥርዓት አላቸውን ? መቁረብ የሚቻለው በጋብቻና በምንኩስና ለተወሰነ ብቻ ነው ? ያለ ጋብቻና ያለምንኩስና መቊረብ አይቻልም? በቅርብ ጊዜ እንደምታስረዱኝ ተስፋ አደርጋለሁ ።

የመጽሔታችሁ አፍቃሪ
ከብካብ መኰንን
ከፍተኛ 11 ቀበሌ 04 ከእንጦጦ
ኪዳነ ምህረት አ.አ.

● በከተማም ሆነ በገጠር ያለች የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የምትመራው በአንድ ሥርዓት ነው ። በአንድ ሲኖዶስ ለምትሠራና በአንድ ፓትርያርክ ለምትመራ ቤተ ክርስቲያን የተለያየ ሥርዓት አይኖራትም ። ስለ ሥጋ ወደሙ አቀባበል ግን ክርስቲያን የሆነ ሁሉ በጋብቻ ወይም በምንኩስና ባይወሰንም ሥጋ ወደሙን ከመቀበል አይከለከልም ። ምክንያቱም ከተጠመቀበት (ክርስቲያን ከሆነበት) ጊዜ ጀምሮ ከሥጋ ወደሙ ተለይቶ መኖር አይገባውምና ነው ። ስለዚህ ክርስቲያን ሁሉ እየቆረበ ኑሮ ሊመነኩስ ወይም ሊያገባ ይችላል ። ጋብቻውም በተክሊልና በሥጋ ወደሙ ይሆናል ። እርግጥ በገጠር እርስዎ እንዳዩት ያልመነኰሱ ወይም በክርስቲያናዊ ጋብቻ ያልተወሰኑ ሲቆርቡ አይታዩም ። ይህም የቤ/ክርስቲያን ሥርዐት ሆኖ ሳይሆን ጉዳዩን ከሚያስረዱ መምህራን እጥረት ነው ።

● ● ●

በየወሩ እየተዘጋጀ የሚቀርብልን ትንሣኤ መጽሔት በጣም የሚያስደስት ነው ። ወደፊትም በበለጠ እንደምትሠሩና ከከተማ እስከ ገጠር ላሉትም ምእመናን ለማዳረስ እስከምትችሉ በርቱ እንላለን ። ከዚህም ጋር ከወንጌል ጥቅስ በመጽሔቱ ላይ ብታቀርቡ ጥሩ ነው ።

በአሁኑ ጊዜ በገጠሪቱ ኢትዮጵያ የሚኖሩ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ካህናት የቤ ክርስቲያን አገልግሎታቸውን እየተው ወደ ልዩ ልዩ ሥራ እየተሠማሩ ናቸው በየአብያተ ክርስቲያኑ የተቋቋመው የሰበካ ጉባኤ ድጐማ እየሰጠ በቤተ ክርስቲያን አገልጋይነታቸው እንዲጸኑ ለምን አይደረግም ?

ስለዚህ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሁሉ ቢያስቡበት መልካም ነው ። ለወደፊቱም ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ እንዲታጣ በየወረዳውና በየአውራጃው መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ቢቋቋም መልካም ነው ።

የድሮ ዲያቆን የዛሬ ወ ር ታዬ ኃ ሚካኤል
9ኛ ክፍለ ጦር 502ኛ ብርጌድ ድሬዳዋ

● ወታደር ታዬ ኃ ሚካኤል በቅድሚያ ስለጻፉልን አስተያየትና ጥያቄ እናመሰግናለን ከከተማ እስከ ገጠር ላሉት ምእመናን የእግዚአብሔርን ቃል ለማዳረስ በተቻለን መጠን ጥረት እያደረግን ነው ፣ ጥረታችን ይሠምር ዘንድ እናንተም ጸልዩልን በመጽሔታችን ራሱን የቻለ የመጽሐፍ ቅዱስ ዓምድ አለ ። ስለዚህ ከወንጌልም ሆነ ከቀሩት ቅዱሳት መጻሕፍት ለአንባቢያን ትምህርት ይሰጣሉ የምንላቸውን በየጊዜው በመጽሔታችን እያሳተምን እናቀርባለን ለወደፊት ግን የወንጌል ትምህርት የሚሰጥበት ዐምድ በመጽሔታችን እንዲኖር ጥረት እናደርጋለን ።

በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ስለሚኖሩ ካህናት ችግር ግን እኛም እንደ እርስዎ የየአብያተ ክርስቲያኑ የሰበካ ጉባኤ አባላትና የቤተ ክህነት ባለሥልጣኖች እንዲያስቡበት መልእክትዎን እያስተላለፍን በበኩላችንም ጉዳዩ አሳሳቢ መሆኑን ከመግለጥ አልቦዘንም ።

● ● ●

ከሁሉ አስቀድሜ በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም

ሠላም ለሁላችን ይሁን 1 በት ሕዝም 30 በቁ. 5 ላይ ፋጥ ሉድም ይላል ይህ አባባል ምን ማለት ነው የትኛውስ ሀገር ነው ።

2 ኦሪ ዘፍጥረት 6=1-4 ላይ የእግዚአብሔር ልጆች የሰውን ሴቶች ልጆች አገቡአቸው ይላል እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች የተባሉት የትኞች ናቸው?

ሀ ብዙ ተባዙ ያለው በጽድቅ እንጂ በኃጢአት አይደለም ስለሆነ ለምን ስለተጋቡ እግዚአብሔር መንፈሱ በሰው ላይ ለዘለዓለም አይኖርም አለ ?

ለ ከሌሎች የተለየ ኃያልነታቸውስ እንዴት ነው ?

ታደለ ማሞ ከወባ መ ድርጅት

● አቶ ታደለ ማሞ ከሁሉ በፊት ክርስቲያናዊ ሰላምታችን ይድረስዎ በትንቢተ ሕዝቅኤል 30፤ 5ላይፋጥሉድየተባሉት 1ኛ ፋጥ ሀ የካም ልጅ ነው ዘፍጥ. 10፡6 ለ በአፍሪቃ ውስጥ ከግብጽ በስተምሥራቅ ያለ ሀገር ነው ዛሬ ስሙ ተለውጦአል ሕዝ.38፡5 ኤር46፡9፡2ኛ ሉድ ፣-ሀ የሴም ልጅ ነው ዘፍ.10፡22 ለ የሀገር ስም ነው የዛሬው ሊብያ እንደሆነ ይገመታል ኢሳ 69 ፡ 19 ኤር 46፡9 ።

በ2ኛው ጥያቄ በዘፍጥረት 6፡1-4 ላይ "የእግዚአብሔር ልጆች" የተባሉ የአዳም ልጅ የሆነው የሴት ዘሮች ናቸው ። የሰው ልጆች የተባሉ ደግሞ የቃ

ወደ ገጽ ፺ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

## ርእሰ አንቀጽ

# መልክአ ክርስቶስ

በእየቤተ ክርስቲያኑ ግድግዳ በእየመጽሐፉ ፡ በእየሠሌዳውና ቅርጻቅርጹ ላይ የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሥዕል ተሥሎ ይታያል ፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ ማን ሣለው ? ማን ቀረፀው ? በምን አይነት መሣሪያ ተሣለ ? በምንስ ዓይነት ሠሌዳ ተቀረፀ ?

አዎ ፡ ስለጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ትክክለኛ ሥዕለ መልክአ እስካሁን ድረስ የሚታወቁት አራት የታሪክ ምንጮች ናቸው ፡፡

1ኛ አብጋሮስ፡ አብጋሮስ ቅድመ ክርስትና 4 ዓመት እስከ 55 ዓመት ድኅረ ክርስትና የነበረ የኤዴሳ (ሶርያ) ንጉሥ ነው ፡፡ አብጋሮስ አንድ ጊዜ ታመመና መድኃኒታችን ክርስቶስ ሄዶ ያድነው ዘንድ ደብዳቤ ጻፈ ፡፡ በደብዳቤውም ውስጥ የጌታን ተአምራት ይዘረዝራል ፡፡ በመጨረሻም "....አንተ ከሰማይ የወረድህ አምላክ እንደ ሆንህ አምናለሁ" ይላል ፡፡ ጌታችንም ለአብጋሮስ መልስ ሲጽፍለት "... ሳያዩኝ የሚያምኑብኝ ብፁዓን ናቸው" ይልና ካረገ በኋላ ከደቀ መዛሙርቶቹ አንዱን ልኮ እንደሚያድነው ተስፋ በመስጠት በመሃረብ መሳይ ጨርቅ ፊቱን ዳስሶ አናንያስ በተባለ ረድእ እጅ ላከለት ፡፡ በዚህ ጊዜ በመለኮታዊ ተአምር መልኩ በጨርቁ ላይ ተቀርጾ ተገኝቶአል ፡፡ (ኤሲብዮስ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ 1 ፡ 13)

2ኛ አብሮቅላ፡- አብሮቅላ ከሠላሳ ስድስቱ ቅዱሳት አንስት አንድዋ ናት ፡፡ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መስቀሉን ተሸክሞ ወደ ቀራንዮ ሲሄድ ቅዱሳት አንስት በኋላ እየተከተሉ ያለቅሱ እንደነበሩ ወንጌላዊ ሉቃስ ያስረዳል ፡፡ ታዲያ ያንጊዜ ከመስቀሉ ክብደት የተነሣ ጌታችን በድካሙ የእኛን ድካመ ነፍስ ያስወግድ ዘንድ በደከመው ና ፊቱ በወዛ ጊዜ አብሮቅላ የተባለችው ቅድስት በሰርሚዶዋ (ቬይል ወይም ሻሽ) ፊቱን ጠረገችው ፡፡ ያንጊዜም መልኩ በሻሹ ላይ ታትሞ ተገኝቷል ፡፡ ይህም ትውፊታዊ ትምህርት በምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት ተቀባይነት ያለው እውነት ነው ፡፡

3ኛ ጢባርዮስ ፡ ከአውግስጦስ በኋላ በ14 ዓ.ም. የተነሣው ቄሣር ጢባርዮስ ይባል ነበር ፡፡ እርሱም ስለ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከጲላጦስ ጋር ደብዳቤ ተጻጽፎአል ፡፡ ጲላጦስም ለጢባርዮስ በጻፈው ደብዳቤ ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መልክአ እንደሚከተለው ይገልጣል ፡፡ "አቅዋመ ሰውነቱ ግርማ ያለው ነው ፡፡ መልኩ አንፀባራቂ ነው ፡፡ ........ቀላ ያለው መልኩና መሐል ለመሐል ተከፍሎ የሚታየው ጠጉሩ የሚሰጠው ውበት ፍጹም ግምት የሌለው ነው ፡፡ የፊቱ ቅርፅ ፡ መልአካውያን ዐይኖቹ የጥቁር ፀጉሩ አወራረድ በሚሰጡት የተንፀባረቀ ውበት ማንም ሰው ቢሆን ለረዥም ጊዜ አትኩሮ ሊመለከተው አይችልም ...." ቄሣር ጢባርዮስ ከጲላጦስ በተገለጠለትና ወንጌላዊ ዮሐንስ የክርስቶስን ትክክለኛ መልክ በሳለለት መሠረት በከበረ ድንጋይ ላይ አስቀርጾታል ፡፡

4ኛ የመግነዙ ጨርቅ ፡- በአሁኑ ጊዜ በኢጣሊያ ውስጥ በቱሪን ካቴድራል የሚገኘው የጌታችንና የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አካል የተገነዘበት ሰንዱን እውነተኛ መልኩን ያየዘ መሆኑ በብዙ ሳይንሳዊ ማስረጃ ተረጋግጦአል ፡፡ የዚህም ዝርዝር ታሪክ በልዩ ልዩ ክርስቲያናውያን መጽሐፎች ከ500 ቋንቋዎች በላይ ታትሞአል ትንሣኤም በቁጥር 31 እትሙ አውጥቶአል ፡ በዚህም እትሙ ብዙዎች ሰዎች ደጋግመው ስለጠየቁ እንደገና አውጥቶታል ፡፡ በመግነዙ ላይ ታትሞ የተገኘው መልክአ ክርስቶስ በአብጋሮስ በአብሮቅላና በጢባርዮስ ዘንድ ከተገኘው መልክአ ጋር አንድነት እንዳለው ታምኖአል ዛሬም የሚታየው የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሥዕል ከዚህ እውነት የተገኘ ነው ፡፡ ከአራቱም ምንጮች የተወሰደው ታሪካዊ መልክአ "ይሤኒ ላህዩ እምውሉደ እጓለ እመሕያው መልኩ ከሰው ልጆች ሁሉ የተዋበ ነው የሚለውን ቃለ ትንቢት አስተርጉሞአል ፡፡



✝

## «በጌታ መግነዝ ላይ የተደረገው ሳይንሳዊ ምርመራ የብዙ ሳይንቲስቶችን ጥርጣሬ አስወገደ»

### የጌታ መግነዝ

በኢጣሊያ ውስጥ ቱሪን ከተማ ላይ የፍሎሬንታይን ቅርፅ ያለው ካቴድራል ይገኛል ፡፡ ከካቴድራሉ ውስጥ 2 ምዕራፍ በሚያህል ርቀት ላይ እጅግ ብዛት ያላቸው ሰዎች በሰልፍ ቆመው ይታዩ ነበር ፡፡ ከካቴድራሉ ውስጥ ደግሞ በመቶ በመቶ ተከፋፍለው መሠውያ በመሰለው ከፍተኛ ሥፍራ ላይ በአስደናቂ ሁኔታ ተቀምጦ በነበረው ጥይት በማይበሳው ሳጥን ዙሪያ በጸጥታ ቆመው የሚታዩ ምእመናን ነበሩ ፡፡

ምእመናኑ በጸጥታና በጥንቃቄ የቆሙበት ምክንያት ነበራቸው ፡፡ ይኸውም ዕራቁቱን ተሰቅሎ የሚታየው የሰው ምስል ያለበት ርዝመቱ 14 ጫማ የሆነ ናይለን ጨርቅ በሳጥኑ ውስጥ ነበርና ያንን ጨርቅ በጥሞና ለማየትና ለመመርመር ነበር ፡፡ ይህ ጨርቅ በቱሪን የሚገኝ ቅዱስ መግነዝ በመባል ይታወቃል ብዙዎችም የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መግነዝ እንደሆነ ያምኑበታል። ይህ ቅዱስ መግነዝ ይላል ኒውስ ዊክ በክርስቲያኑ ዓለም ውስጥ ስለ ጌታ ከሚቀርቡት ማስረጃነት ካላቸው ማስታወሻዎች መካከል በቅድስናውና በአሳማኝነቱ ከሁሉም የበለጠና በተለይ ዘመናዊውን ሳይንስ ያስጨነቀና ለሳይንቲስቶችም ትልቅ ፈተና ሆኖ ተገኝቷል ፡፡ ያ እጅግ ብዛት የነበረው ሕዝብ የተሰበሰበት ምክንያት መግነዙን ለማየት ቢሆንም በተለይ ደግሞ መግነዙ ቱሪን ከተማ የደረሰበትን 4 መቶኛ ዓመት ለማክበር ነበር ፡፡ በበዓሉ ምክንያት ተሰብስበው መግነዙን እያዩ ያለፉት ሰዎች 3 ሚሊዮን ነበሩ ፡፡ እነዚህ ሰዎች ስለ መግነዙ የተለያዩ አስተያየቶች ሰጥተዋል። ለምሳሌ አንዲት የእስቴን መነኩሲት በመግነዙ ላይ የጌታን ምስል ለማየት ችያለሁ" ሲሉ ሌላው የፈረንሳይ የ18 ዓመት ወጣት ደግሞ "መግነዙን ከማየት በቀር በላዩ ምንም አይነት ነገር ማየት አልቻልኩም" ብሏል ፡፡ ስለዚህ በመግነዙ ላይ ያለው ምስል የሚታያቸው ፤ /የማይታያቸውም አሉ ፡፡

የቱሪኑ ጳጳስ ፈቃድ ከሰጡ የዓለም አቀፍ ሳይንስ የሊቃውንት ቡድን በመግነዙ ላይ የተራቀቁ የሳይንስ ምርምሮችን ለማካሄድ በቅርቡ ሥራውን ይጀምራል ፡፡ እነዚህ ሳይንቲስቶች በሚያካሂዱአቸው ረቂቅና ከባድ ምርመራዎች መሠረት የዚህን አስደናቂ መግነዝ ምንነትና ምስጢር መግለጽ እንደሚችሉ ተስፋ ያደርጋሉ ፡፡

ከአሁን በፊት የተካሄዱት ምርመራዎች በአንድ አንድ ሳይንቲስቶች አእምሮ የነበረውን ጥርጣሬ ለማስወገድ ችሎአል ፡፡ የመግነዙ መርማሪ ቡድን መሪ የሆኑት አሜሪካዊው የሳይንስ ሊቅ ኬኔት ስቲቨንስን እስካሁን ያደረጉአቸውን ሳይንሳዊ ምርመራዎች መሠረት በማድረግ ሲናገሩ "ከቡድኑ መካከል አብዛኞቻችን መግነዙ ትክክል የጌታ መግነዝ መሆኑን እናምንበታለን" ብለዋል።

መቸም ለማዕከላዊው ተመልካች ማየት የግድ ማመን አይሆንም መግነዙ በዓይን ሲታይ በ16ኛው ምእት ዓመት በደረሰው ኃይለኛ የእሳት ቃጠሎ ምክንያት ሁለት ጐን ለጐን የሚታዩ ቀጥተኛ መስመሮች በመግነዙ መካከል የሚታየውን የሰው ምስል እያዋሰኑ ከላይ ወደታች ይወርዳሉ ፡፡

ከሰማንያ ዓመታት በፊት የመጀመሪያውን ፎቶግራፍ ያነሱ ኢጣሊያዊ የሕግ ሊቅ ሲናገሩ መግነዙ የፎቶግራፍ ፊልም እንደሚመስልና ፎቶግራፍ በሚነሣበት ጊዜ ነጋቲቩ ጥርት አድርጐ የሚያሳይ ፖዘቲቭ የሆነ ምስል እንደሚሰጥ ገልጠው ነበር ፡፡

ትላልቅና ጎላ አድርገው የሚያሳዩ ነጋቲቭ ፊልሞች ከካቴድራሉ ክልል ተዘርግተው ቁመቱ 5 ጫማ ከ11 ኢንች የሆን ያረፈ ወይም ያንቀላፋ የሚመስል እጆቹ በወገቡ አጥንት ላይ ዘና ብለው ተዘርግተው ሁለት እግሮቹም በቁርጭምጭሚቱ ላይ ተደራርበው እንዳለ የሚያሳይ ምስል ይዘው ይገኛሉ ፡፡

ይህ ሰው ረዥም ፅህም እንደነበረው ይታያል ፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ በተገለጠው የዕብራውያን ልማድ መሠረትም በምስሉ ላይ ፀጉሩ ተጐንጉኖ ይታያል ፡፡ የዚህ ምስል ሁኔታ ለሐኪሞችና ለሰው አካል አጥኚዎች አስደናቂ ሆኖ ተገኝቷል። በወንጌሉ ውስጥ በተገለጠው ሁኔታ በመገረፉና በመቸንከሩ ምክንያት ቁስልና ሰንበር በፊቱና በሌላው የአካል ክፍሉ ይታይበታል ፡፡ ይህም በወንጌል ውስጥ ከተጠቀሰው የመገረፍ የመደብደብና የመቸንከር ሁኔታ ጋር በትክክል ይመሳሰላል ፡፡

ሁለቱ ትከሻዎቹ ከባድ መስቀል እንደ ተሸከመባቸው የሚያሳዩ ምልክቶች ይታዩባቸዋል ፡፡ እጆቹና እግሮቹም እንደ ተቸነከሩ የሚያሳይ ምልክት ይገኙባቸዋል ፡፡ በ5ኛውና በ6ኛው የጐን አጥንቱ መካከል ያለው ቦታም በጦር ተወግቶ እንደ ቆሰለ ያሳያል ፡፡ ይህ በመግነዙ የሚታየው ምልክት ይህ ሁሉ ሥቃይ መወጋትና ግርፋት የደረሰበት ሰው በዚያን ጊዜ ከነበረው ሮማዊ ወንጀለኛ የተለየ የሚያደርገው ማስረጃ ሆኖ



www.ethiopianorthodox.org

ተገኝቷል ። ይኸውም በራሱ ላይ በተደፋለት የእሾህ አክሊል ምክንያት የፈሰሰው ደም በራሱ ፀጉር ተረጭቶና በግንባሩ ላይ ወርዶ መገኘቱ ነው ። በዚያጊ ዜ የነበረው ሮማዊ ወንጀለኛ ግን ምንም ግርፋትና ስቃይ ቢደርስበትም እንዲህ ዓይነት ደም አይታይበትም ።



በመግነዙ ላይ ተቀርፆ የተገኘው የጌታችን ሥዕል

## አምላካዊ አካል ከመግነዙ በታች

በመግነዙ ላይ ይታያል የሚባለው ምስል የተራቀቀ የሥዕል ችሎታ የነበራቸው ክርስቲያኖች አስመስለው ሌላውን ለማሳመን የሳሉት ሊሆን ይችላል የሚል ጥርጣሬ በሳይንቲስቶችና በታዛቢዎች ልቦና ሲጉላላ ቆይቶአል ።አሁን ግን በተደረገው ሳይንሳዊ ጥናትና ምርምር መሠረት ምንም የሰዓሊ እጅ ወይም የሰዓሊዎች ቀለም እንደ አላረፈበት ተረጋግጦአል ። በተጨማሪ ይህ ንዐይነት ሥዕል ለመሳል በዚያን ጊዜ የአናቶሚና የፖቶሎጂ ምሥጢርን ጠንቅቆ ያወቀና የፎቶግራፍ ጥበብም አጠናቅቆ ያጠና ሰው መኖር ነበረበት ። ግን እንዲህ ዓይነት ሰው ጌታ በተሰቀለበት ጊዜ ፈጽሞ ሊኖር አይችልም ። ምክንያቱም የፎቶግራፍ ጥበብ የታወቀው ከስቅለት በኋላ 500 ዓመታት ቆይቶ ነው ። ስለዚህ የፎቶ ግራፍ ሕግና ጥበብ ያወቀ ሰው ካሜራ ከመሥራቱ ከ 500 ዓመታት በፊት ነበር ብሎ ማሰብ ፌዝ ሆኖ ይቀራል ።

ከዚህም ሌላ ከአሜሪካ የጠፈር ምር ምር ድርጅት በተገኘው የሥዕል መመርመሪያ መሣሪያ ምስሉ ተመርምሮ እንዲህ አይነት ከ3 አቅጣጫ ሊታይ የሚችል ሥዕል ወይም ምስል በቀለም ወይም ሁልጊዜ በምንጠቀምበት ካሜራ መሳል እንደማይቻል ተረጋግጦአል ። የታወቁት አሜሪካዊ ሳይንቲስት ስቲቨንስን ሲናገሩ "ባደረግነው ምርመራ መሠረት እንዲህ ዓይነት ምስል በፎቶ ግራፍ ጥበብ ወይም በእጅ ለመሳል ለዚያ ጊዜ ሰው እንደማይቻል አረጋግጠናል" ይላሉ·

ስለምስሉ በዚህ እናቁምና ወደ መግነዙ እንሂድ መግነዙ ስንት ዓመታት አልፈውት ይሆን ? ከየትስ መጣ? መግነዙስ ላይ የሚታየው ምስል ሰው ካልሳለው/ጨርቁ ላይ እንዴት እንደ ማኅተም ሊታተም ቻለ? የሚሉ ጥያቄዎች በእያንዳንዱ አእምሮ ሲጉላሉ ቆይተዋል።እስቲ ለእነዚህ ጥያቄዎች የሚቀርቡትን መልሶች እንመልከት ።

የተረጋገጡ የታሪክ ማስረጃዎች እንደሚገልጹት ይህ መግነዝ በ14ኛው ምእት ዓመት በፈረንሳይ አገር ጂኦፈሪ የሚባል የፈረንሳይ ሰው ሚስት የነበረችውና በኋላ መበለት የሆነችው የፈረንሳይ ሴት አማካይነት ለትርኢት ይቀርብ ነበር ። በአካባቢው ይኖሩ የነበሩ ጳጳስ ግን የዚህ መግነዝ ነገር በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሰ ስላልሆነ እንዳይታይ ብለው ከለከሉ ።

በቅርቡ በመግነዙ ላይ የተካሄዱት ሳይንሳውያን ምርመራዎች ጌታ በነበረበት ጊዜ በእሥራኤል ይሰራ እንደነበረው የልብስ ዓይነት መሆኑን አረጋግጠዋል ፤ በተለይም የስዊዙ የወንጀል ጉዳይ ምርምራ ሊቅ የሆኑት ማክስ ፍራይ ከመግነዙ ደቃቅ ብናኞች በመውሰድ ለ9 ዓመታት ጥናትና ምርመራ ካካሄዱ በኋላ ጌታ በነበረበት ዘመን በሙት ባሕር አካባቢ ይገኝ ከነበረው የጨርቅ ዓይነት ጋር አንድ መሆኑን ወይም ተመሳሳይነት ያለው መሆኑን ገልጠዋል፡ በበኩሌ ይላሉ ማክስ ፍራይ "የጌታ መግነዝ መሆኑን ለማመን ችያለሁ በምርመራው መሠረት መግነዙ 2000 ዓመታት ያህል ሆኖታል " ።

## ትክክለኛ ተመሳሳይነት

መግነዙ ከየት ተነስቶ ወዴት እንደ ሄደና ማን እንደወሰደው በጣም በታወቁት እንግሊዛዊው የታሪክ ሊቅና ጋዜጠኛው ዊልሰን የተሰጠው ማብራሪያ በስዊዙ የወንጀል ምርመራ ሊቅ በተሰጠው የምርመራ ውጤት ተጨማሪ ድጋፍ አግኝቶአል ።

"የቱሪኑ መግነዝ" በተባለው በቅርቡ ታትሞ በወጣው መጽሐፍ እንግሊዛዊው ዊልሰን የሚከተለውን ጽፈዋል። ይህ መግነዝ ከጌታ መልክ ጋር ትክክለኛ ተመሳሳይነት ያለው ምስል የያዘ ተአምራታዊው ልብስ/ሰንዱናት ብለው የምስራቅ ኦርቶዶክስ ምእመናን ያምኑበት የነበረው ነው ይላሉ ። የታሪክ ሊቅና ጋዜጠኛው ዊልሰን ይህ መግነዝ ከእስራኤል በቱርክ ውስጥ ወደምትገኘው አደሳ ወደ ተባለችው ከተማ አንድ ሐዋርያ ከ50 ዓ.ም. በፊት በከተማዋ ወደነበረው የክርስቲያን ንጉሥ ወስዶ በስጦታ መልክ እንደአበረከተለት በአንዳንድ ማስረጃዎች በመደገፍ ይገምታሉ ። ከተማዋ በአረማውያን እጅ እንደ ወደቀች ግን መግነዙ እስከ 6ኛው ምእት ዓመት ጠፍቶ ቆይቶ ነበር ።በኋላ ግን በከተማዋ ቅጥር በነበረው ዋሻ መገኘቱን ዊልሰን በጻፉት መጽሐፍ ተገልጾአል ። ይህ መግነዝ በ944 ዓ.ም እንደገና ከአደሳ ወደ ቁስጥንጥንያ ተወስዶ በጊዜው በነበረው ክርስቲያን መሪ ግምጃ ቤት ውስጥ እንደተቀመጠም ዊልሰን ገልጸዋል በዚያ ጊዜ የቁስጥንጥንያ ሰዎች በመግነዙ የነበረው ምስል ከአንገት በላይ ብቻ እንጂ ከራስ እስከ እግር የሚያሳይ መሆኑ እንዳልገባቸው ዊልሰን ያምናሉ ። ይህም የሚታወቀው በዚያ ጊዜ መግነዙ ለትርኢት ሲቀርብ ታጥፎ ከአንገት በላይ ያለው ምስል ብቻ እንዲታይ መደረጉ ነው ። ዊልሰን በተጨማሪ ሲያብራሩ ከ6ኛው ምእት ዓመት በኋላ የተሳሉት የጌታ ስዕሎች ተመሳሳይ የሆኑበት ምክንያት በመግነዙ ምስል መሠረት ተነድፈው ስለተሳሉ ነው ይላሉ ። መግነዙ ከቁስጥንጥንያ በጂኦፈሪ አባት ወደ ፈረንሳይ መወሰዱን በኋላም የጂኦፈሪ ሚስት የነበረችው መበለት በ14ኛው ምእት ዓመት ለሕዝቡ ማሳየቷን ቀጥሎም የሀገሩ ጳጳስ እንዳይታይ መከልከላቸው በዚሁ መጽሐፍ ተጠቅሶአል በመጨረሻ በ1453 ዓ.ም. መግነዙ ከፈረንሳይ ወደ ሮም በበጎ ፈቃድ እንዲሄድ ተደርጎ አሁን ካለበት ይገኛል ሲሉ የታሪክ ሊቁ ዊልሰን ደምድመዋል ።

## አንፀባራቂው ብርሃናዊ ኃይል

በዘመናዊው የሳይንስ ጥበብ መሠረት የመግነዙን እድሜ ለመለካት ከተፈለገ የካርቦን 14 ፈተና በመግነዙ ላይ ማካሄድ ነው ። ግን ይህ ዓይነቱ ፈተና መግነዙን በጣም ሊያበላሸው ስለሚችል በዚህ ምክንያት የቤተ ክርስቲያን ባለሥልጣኖች ምርመራው እንዳይካሄድ ከልክለው ቆይተዋል ። አሁን ግን የአሜሪካ የሳይንስ ሊቃውንት 5 ሚሊ ሜትር የምታህል ቁራጭ ከመግነዙ ወስደው የካርቦን 14 ምርመራ ለማድረግ ተዘጋጅቷል ።

ሌሎች ሳይንቲስቶች ደግሞ በአንድ የሰው ፀጉር ላይ ብቻ 30 የሚሆኑ ንጥረ ነገሮችን ማግኘት በሚችል አዮን ማይክሮፕሮብ በተባለው መሣሪያ በመግነዙ ላይ ምርመራ አካሂደው ምስሉ ምንም ዓይነት የስአሊ ቀለም ያልነካው መሆኑን ለማረጋገጥ ተስፋ ያደርጋሉ።የኒውትሮን አክቲቪሽን ምርመራ ደግሞ በመግነዙ ላይ በእርግጥ የሰው ደም መኖሩን ለማረጋገጥ የሚችል መሆኑ ታውቋል። በተጨማሪ የራጂ ምርመራ ፣ የፎቶ ማይክሮግራፍ ሊተጣጠፍ በሚችል መነጽራዊ መሳሪያዎች በመጠቀም የተለያዩ ምርመራዎችን ለማካሄድ እቅድ አላቸው ።

በመግነዙ ላይ የሚታየው ምስል የሰው እጅ ካልተጠበበበት ታዲያ ምን ዓይነት ኃይል ወይም ጥበብ በመግነዙ ላይ አትሞት ይሆን? የሚለው ጥያቄ እስካሁን ለአንድ አንድ ሳይንቲስቶች እንቆቅልሽ ነው ። ለክርስቲያኖች ግን እንቆቅልሽ አይደለም ።

ሌላ ምክንያት ሲጠፉ ሳይንቲስቶች ያቀረቡት የእንቆቅልሽ መልስ እንዲህ ይላል ።"ይህ ምስል በመግነዙ ሊታተም የቻለው አንፀባራቂ በሆነው ብርሃናዊ ኃይል ራድያንት ኢነርጂ ነው ። ይላሉ ። አሜሪካ ውስጥ በሚገኘው በሎስ አለምስ ማዕከላዊ የሳይንስ ለቦራቶሪ የሚሠሩትና መግነዙን ከሚመረምሩት ሊቃውንት አንዱ የሆኑት ተርማል ኬሚስት (የእሳታዊ ቅመማ ሊቅ) አሜሪካዊው ሬይጀርስ ሲያብራሩ"ምስሉ የታተመው በኃይለኛ ብርሃናዊ ነፀብራቅ ፍንዳታ/ አማካይነት ነው" ይላሉ ። ይህ አንፀባራቂ ብርሃን የተባለው ጌታ ከሙታን ሲነሣ ተጐናጽፎት የነበረውን ብርሃን መለኮት እንደሚያመለክት ንዊስ ዊክ ይጠቁማል ።

አንዳንድ መናፍቃን ጌታ በእርግጥ በቀድሞው አካሉ ከሙታን ተነሥቷል ብለው አፍ ሞልተው ለመናገር በሚያፍሩበት ጊዜ እንዲህ አይነት የሳይንስ ምርምር የደገፈው አሳማኝ ነገር መገኘቱ ወቅታዊ ነው ይላል ሳምንታዊው መጽሔት /ኒውስ ዊክ/ መጽሔቱ ይቀጥልና በጌታ ትንሣኤ ተጠራጥሮ የነበረው ሐዋርያ ቶማ ስም እኮ በጦር የተወጋውን የጌታን የማናይ ገቦ በእጁ በዳሰሰው ጊዜ ነው ያመነው ። እንደዚሁም ሁሉ ይህ የጌታ መግነዝ ትክክለኛነቱ በሳይንስ ምርመራዎች ጭምር ከተረጋገጠ የዛሬ ቶማሶች እምነታቸው ተጠናክሮ ሐዋርያዊው ተልእኮአቸው በበለጠ ይፋፋማል ይላል ።



ታሪኩን ተርጉሞ ያቀረበልን
ጸጋዬ ተፈራ

የሃይማኖተ አበው የኢትዮጵያ ተማሪዎች መንፈሳዊ ማኅበር አባልና የ መጨረሻ ዓመት የዩኒቨርሲቲ ተማሪ ነው፡ ታሪኩም የተተረጐመው መስከረም 18 ቀን 1978 ዓ.ም. (እ.ኤ.አ.) ከታተመው ኒውስ ዊክ ከተሰኘው ሳምንታዊ መጽሔት ነው ።







www.ethiopianorthodox.org

# ጴጥሮስ በሮም አደባባይ

«ጌታ ወኅኒም ወደ ሞትም ከአንተ ር ለመሄድ የተዘጋጀሁ ነኝ» የመ መሪያዎቹ ክርስቲያኖች እስራት ወ ም ሞት ከክርስቶስ ፍቅር እንደ ማይ ያቸው በመዝሙርና በሃይማኖት መ መሪያ ቃል ያረጋግጡ ነበር ። እርግጥ ለ ክርስቶስ ስም መስክረው ለመሞት ንጂ እንደ ወንጀለኛ በማያገባቸው ዳዩ ገብተው ታስረውና ተደብድበው መሞት አይሹም ነበር ። ስለዚህ ነው ዱስ ጴጥሮስ መድኃኒታችንና ጌታ ችን ክርስቶስ በተያዘበት ሌሊት «ወደ ወኅኒም ወደ ሞትም ከአንተ ጋር ለመ ሄድ የተዘጋጀሁ ነኝ» ሉቃ. ፳፪-፴፫ ሲ ል በድፍረት ቃል የተናገረው ጴጥሮስ ለማሰብና ለመናገር ለመጠየቅና መል ስ ለመስጠት እጅግ ፈጣን የሆነ አእም ሮ ነበረው ።

ከዚህም የተነሣ በሐዲስ ኪዳን ውስጥ ብዙ ጥያቄዎችን እንደ ጠየቀና ጌታ ለአቀረባቸው ጥያቄዎች ሁሉ መልስ እንደሰጠ ተጽፏል ። በድፍረትና በቀል ጠፋነት ብዙ ተግባሮችን ፈጽሟል ፤ ለምሳሌ ጌታ በባሕር ላይ ሲሄድ አይቶ እርሱም ለመሄድ ሞከረ የሚይዙት ጭፍሮች እንደሚመጡና ደቀ መዛሙርቱም እንደሚከዱት ጌታ በተናገረ ጊዜ «ሁሉ ቢከዱህ እኔ አልከድህም» ሲል በወኔ መንፈስ ተናገረ ፤ ወዲያውም ጭፍሮች ከመጡ በኋላ ሰይፍ ወርውሮ የአንድ ሰው ጆሮ ቆረጠ ።

ጴጥሮስ ይህ ዓይነት የድፍረት ጠባይ እስከ መጨረሻ ስለ አልተለየው ቄሣር ኔሮን ሮምን ያስተዳድር በነበረበት ጊዜ ፤ በክርስቲያኖች ላይ ይፈጸም የነበረውን አሰቃቂ ሥቃይ ምንም ሳይፈራ በሮም ከተማ ወንጌልን እስተማረ ብዙ ማኅበረ ክርስቲያንንም በሮም አደራጀ ። በማኅበረ ክርስቲያኑም ውስጥ የብዙ ባለሥልጣኖች ቤተሰቦች ይገኙበት ነበር ። ለምሳሌ የኔሮን ባለሟሎች የነበሩ የአግሪጳና የአልቢኖስ ቤተሰቦች በጴጥሮስ ትምህርት ተስበው በክርስቶስ አምነው ነበር ። በዚህም ምክንያት አግሪጳና አልቢኖስ ጴጥሮስን እንዴት እንደሚያስገድሉ ምቹ ቦታና ጊዜ ይፈልጉ ነበር ። ነገር ግን የአልቢኖስ ሚስት በጴጥሮስ ላይ የተመከረውን ምክር ስለሰማች ሄዳ ለክርስቲያኖች ተናገረች ። ክርስቲያኖችም ጴጥሮስን እንዲሸሽ ለመኑት ፤ እርሱም ከብዙ ልመና በኋላ እሽ ብሎ የሮምን ከተማ ቅጥሮች እንደ ወጣ ክርስቶስ ተገለጸለት ፤ ጴጥሮስም «ጌታ ሆይ ወዴት ትሄዳለህ» ብሎ ቢጠይቀው «እንደገና ለመሰቀል ወደ ሮም እሔዳለሁ» ብሎ መለሰለት ።



ጴጥሮስ በሮም አደባባይ ለቀልቀሊት የተሰቀለበትን መስቀል እንደተሸከመ

ጴጥሮስ ይህን ሰምቶ በጥልቅ መንፈሳዊ ስሜት ስለ ተነካ ወደ ሮም ተመለሰ። አሁን ጴጥሮስ «ወደሞትም ቢሆን ከአንተ ጋር ለመሄድ የተዘጋጀሁ ነኝ» በማለት የተናገረው ቃል ሊፈጸም ተቃረበ ። ክርስቲያኖች ሁሉ ጴጥሮስ እንደ ተመለሰ አይተው ተላቀሱ ምክንያቱም ያንጊዜ በሮም በክርስቲያኖች ላይ ይካሄድ የነበረው መከራ እጅግ ያሰቅቅ ነበርና ። ለምሳሌ ክርስቲያኖች በርጥብ ቆዳ ተጠቅለው ለለማዳ አንበሶች ይጣሉ ነበር ፤ ሰምና እዶሮማ ር ሌላም የሚያቃጥል ቅባት ተቀብተው እንደ ጡዋፍ ከእንጨት ጋር ታስረው በየመንገዱበየአደባባዩናበየትያትርቤቱበሌሊት እንዲያበሩ ይቃጠሉ ነበር ። ይህ ብቻ አልነበረም በሮም የስፖርት ሜዳ ላይ ከአንበሳ ጋር እየታገሉ ሲወድቁ ይስቁባቸው ሲጥሉ ግን ይደ በድቧቸው ነበር ። ይህንና የመሳሰለውን መከራ ሁሉ የተመለከቱ ክርስቲያኖች በጴጥሮስ ወደ ሮም መምጣት እጅግ አዘኑ ። ይሁን እንጂ በክርስቶስ ፍቅር የሰከረው ጴጥሮስ ወደኋላ አላለም የኔሮንን ቁጣ ፤ የአግሪጳንና የአልቢኖስን ዛቻ አልፈራም የአንበሶች ትግል የእሳቱ ነበልባል አላስበረገገውም ይልቁንም እንዴት መሞት እንደሚገባው ለገዳዮቹ መግለጫ ለመስጠት ያስብ ነበር እንዲህ በዚህ ሳለ ቀኑ እንደ ኢትዮጵያ ቤ ክርስቲያን ሐምሌ ፭ ቀን ፶፰ ዓ.ም. እንደ ላቲን ቤ ክርስቲያን ግን ሰኔ ፳፱ ቀን ፷፭ ዓ.ም. ቄሣር ኔሮን የክርስቲያኖች. መሪ (መምህር) ተይዞ ወደ ሮም አደባባይ እንዲሄድ አዘዘ ። በሀገራቸው ከሰኔ ጀምሮ የበጋ ወራት ነው ። ሕዝቡ ሁሉ ፀሐይ ለመሞቅ ጨዋታ ለማየት ወደ አደባባይ ይወጣል

ጴጥሮስ ወደዚያ ሁሉ ሕዝብ የፊጥኝ ታስሮ በጭፍሮች ተከቦ እየተገፋ ሄደ መሰቀያም ተዘጋጅቶለት ስለነበር ጴጥሮስ መስቀሉን ባየ ጊዜ «እንደ ጌታዬ

ወደላይ አትስቀሉኝ ግን ራሴን ወደ ታች አድርጋችሁ ስቀሉኝ» አለ ። እነርሱም እንደነገራቸው አድርገው ሰቀሉት በዚህ ጊዜ ከአንተ ጋር ለሞት የተዘጋጀሁ ነኝ ያለው ቃሉ ተፈጸመለት ። ከዚህም በፊት በ፴፯ ፵፫ ዓ.ም. በኢየሩሳሌም ከተማ ታስሮ ስለነበር ለእስራት የተዘጋጀሁ ነኝ ያለው ቃሉ ተፈጽሞለታል ። እነሆ ቅዱስ ጴጥሮስ በጻፋቸው መጻሕፍት ብቻ ሳይሆን እስከ መስቀል ድረስ ባደረገው ድፍረት ትዕግሥትና ቆራጥነት ታላቅ መልእክት አስተላልፏል ። እዎ የቀደሙን ሁሉ በእምነታችን እንዴት መጽናትና መመስከር እንደሚገባን እርአያነታቸውን ትተውልን አልፈዋል ፤ ጴጥሮስ በሮም አደባባይ ቢገደልም የክርስትና እምነት ከሮም አልጠፋም ይልቁንም ሮም በዓለም ካሉት ከ፫ ታላላቅ አብያተ ክርስቲያናት የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን መዲና ሆነች ዛሬም የሰባት መቶ ሚሊዮን የካቶሊክ ክርስቲያኖች ርእስ በጴጥሮስ መቃብር ላይ በተቆረቆረችው በቫቲካን ከተማ ይኖራል ። ከዚህም ሌላ ቅዱስ ጴጥሮስ በዓለም ባለች ሁሉ ቤ ክርስቲያን የሚከበር ዓለም አቀፍ ቅዱስ ሐዋሪያ ነው። የኢትዮጵያ እርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም በየዓመቱ ሐምሌ ፭ ቀን በታላቅ ሥርዓት ታከብረዋለች ። እውነተኛ የወንጌል መምህር የእምነት ምስክር ስለክርስቶስ ፍቅር ቆራጥና ደፋር ታላቅ ሐዋርያ ነውና ።


ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ

## ደብዳቤዎች .....

ከገጽ ፩ የዞረ

ኤል ዘሮች ናቸው ሴት የእግዚአብሔር ሰው ሲሆን ቃየል ግን ዓመጸኛ ሰው ነበር ። የእግዚአብሔር ልጆች ተብለው የተጠሩ የሴት ዘሮች የዓመጸኛውን የቃየልን ልጆች ስላገቡ "የእግዚአብሔር መንፈስ በሰው ላይ እንደማይኖር ተነገረ ጋብቻ በመሠረቱ ኃጢአት አይደለም ። ግን ምኞትን ብቻ ለመፈጸም የሚደረግ ከሆነ ከጽድቅነቱ ይወጣል ።

ከሴት ዘሮችና ከቃየል ዘሮች የተወለዱ ልጆች ኃያላንና ታላላቅ እንደነበሩ እርስዎ በጠቀሱት ምዕራፍና ቁጥር ተገልጦአል ስማቸውም ኔፊሊም ይባላል ይህም በመጀመሪያ ጊዜ ማንኛውም ፍጥረት ታላቅና ኃያል እንደነበረ ያመለከታል እንጂ ልዩ ፍጥረት ከሰዎች ጋር ስለተገናኙ ጉድ ወለዱ ማለት አይደለም ። እርግጥ እነዚህን ኃያላን ሰዎች (ኔፊሊም) የወደቁ መላእክት ናቸው ብለው የሚተረጉሙ አንዳንድ ሊቃውንት አይታጡም "ትንሣኤ ግን በዚህ ሀሳብ አይስማማም ።





www.ethiopianorthodox.org

# ሰላማ ከሣቴ ብርሃን (ከ330-352)

"ዝንቱሰ ብእሲ መምህርነ
ዘተፈነወ ውስተ ምድርነ
ይከሥት ብርሃነ"

ብርሃንን ይገልጥ ዘንድ ወደ ሃገራች የተላከ ይህ ሰው መምህራችን ነው። ቅዱስ ያሬድ ድጓ) እውነተኛ የዓለም ብርሃን ራሱ መድኃኒታችን ክርስቶስ ብቻ ነው ። ግን በክርስቶስ አምነው ክርስቶስን የዓለም ብርሃንነት ለዓለም የሳወቁ ሁሉ "ብርሃናተ ዓለም ተብለዋል" ሐዋርያት ብርሃናተ ዓለም እንደሆኑ በወንጌል ተጽፎአል ። (ማቴ 5፡14 በዚህም አንፃር የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ሐዋርያ ቅዱስ ፍሬምናጦስ "ከሣቴ ብርሃን" ወይም ብርሃነ ኢትዮጵያ እየተባለ ይጠራል ። እንዲህም የተባለበትን ምክንያት ለመግለጥ ታሪኩን በአጭሩ እንመለከታለን ።

ፍሬምናጦስ

ስለ ክርስትና እምነት ወደ ኢትዮጵያ መግባት ሦስት የተለያዩ ታሪኮች አሉ ።

1. በኢትዮጵያዊው ጀንደረባ
2. በሐዋርያው ማቴዎስ
3. በፍሬምናጦስ ጊዜ እንደገባ ይተረካል ። ሁሉም እውነት እንደሆነ በታሪክ አዋቆች ተረጋግጦአል ። ግን ክርስትና የሀገሪቱ እምነት የሆነው ና ከእነ ሙሉ ሥርዐቱ የተሰበከው በፍሬምናጦስ ሐዋርያነት ጊዜ ነው ።

በ330 ዓ.ም.፦ ሜሮጵዮስ የተባለ ጢሮሳዊ ነጋዴ ፍሬምናጦስና ኤዴስዮስ ከተባሉ ሁለት ወጣቶች ልጆቹ ጋር ወደ ኢትዮጵያ መጣ ። በዚያ ጊዜ የኢትዮጵያ ወደብ ወደነበረው አዱሊስ እንደ ደረሰ ዕቃውን ከመርከቡ አውርዶ ከሁለቱ ልጆቹ ጋር የእግር መንገድ ጀመረ ። ያንጊዜም ለገንዘቡ የሳሱ ሽፍቶች ሜሮጵዮስን ገደሉት ። ነገር ግን ልጆቹን ከመግደላቸው በፊት ባላገሮች ደርሰው አዳኑአቸው ከዚህ በኋላ ወጣቶቹን ወደ ባሕረ ነጋሽ ወሰዱአቸው ።

ባሕረ ነጋሽም እልዓሚዳ ወደተባለው ወደ አክሱም ንጉሥ ላካቸው ። እነሱም በምን ምክንያት እንደ መጡ እንዴትስ አደጋ እንደ ደረሰባቸው ለንጉሡ ተናገሩ አልዓሚዳም ራርቶ የበጎነት ሥራ አደረገላቸው ከጥቂት ጊዜ በኋላ አልዓሚዳ ሞተ አሕየዋ የተባለች ባልተቤቱ ለልጆችዋ ሞግዚት በመሆን የመንግሥትን ሥራ ማካሄድ ጀመረች በዚህ ጊዜ ለኤዴስዮስ የጸሐፊነት ለፍሬምናጦስ የቤተ መጻሕፍት ኃላፊነትና የልጆች አስተማሪነት ማዕረግ ሰጠች ።

ፍሬምናጦስ ስለወንጌል ትምህርት ንቃት ያለው ሰው ነበርና የክርስትናን እምነት ለቤተ መንግሥት ልጆች ሁሉ አስተማረ በአክሱም ከነበሩት ካህናተ አሪትም ጋር ግንኙነት እያደረገ ጥቂት በጥቂት የክርስቶስን ብርሃን ይገልጥላቸው ነበር ።

ከዚህም በኋላ ኤዛና የተባለው ትልቁ ልጅ አድጎ የአባቱን ሥልጣን በያዘ ጊዜ ኤዴስዮስ ወደ ሀገሩ ወደ ጢሮስ ተመለሰና ካህን ሆኖ ኖረ ፍሬምናጦስ ግን በስንብት ወደ እስክንድርያ ሄዶ የኢትዮጵያ ሕዝብ ወንጌልን የሚሰብክና የሚያጠምቅ መምህር እንደሚፈልግ በዚያ ጊዜ ለነበረው ሊቀ ጳጳሳት ቅዱስ አትናቴዎስ አመለከተ ። ቅዱስ አትናቴዎስም በእግዚአብሔር ፍቅርና በመንፈሳዊ ቅንዐት ትጋት ያለው እንደዚሁም የሀገሩን ቋንቋና የሕዝቡን ልማድ የሚያውቅ ከቅዱስ ፍሬምናጦስ በቀር ሌላ ሰው አለመኖሩን ተገንዝቦ ሢመተ ጵጵስናን ሰጠውና ወደ ኢትዮጵያ ላከው ።

ሰላማ

ፍሬምናጦስ ይባል የነበረው ጵጵስናን ሲቀበል ሰላማ በመባል ተሰይሞአል ። ይህ ስያሜ ሰለማ በክርስቶስ መስቀልና ደም በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ስለተፈጸመው የእርቅ ሥራ ለሕዝበ ኢትዮጵያ አብሣሪ መሆኑን ያመለክታል ። ሰላማ መዓርገ ጵስናን ተቀብሎ ወደ ኢትዮጵያ መጣ ። በፊት ሰላማ ያስተማረው ኢዛና ከአባቶቹ ተያይዞ የመጣውን ልማድና አምልኮ ፈጥኖ ለመተው የሚያዳግቱትብዙ ምክንያቶች ቢኖሩምእንኳአቡነሰላማወንጌሉንገልጦባስተማረጊዜአመነናተጠመቀ።ስሙም አብርሃ ተባለ ሳይዘናስ የተባለው ወንድሙም አጽብሐ በመባል ተሰየመ ። ከካህናተ አሪትም ብዙዎቹ በክርስቶስ ስም አመኑ በልዩ ልዩ አምልኮ የኖሩ አረማውያን ደግሞ አምልኮተ ባዕድን ና ክፉ ልማድን እየተው በክርስቶስ አመኑ ።

ከሣቴ ብርሃን

አቡነ ሰላማ የአሪት ቀንበርና የአሕዛብ ልማድ አጨልምአት የነበረችው ኢትዮጵያን በብርሃነ ወንጌል ስለአበራት በብርሃነ ትምህርቱ የተደሰቱ ኢትዮጵያውያን "ሰላማ ከሣቴ ብርሃን" ሲሉ ሥራውን ጨምሮ የሚገልጥ የክብር ስም ሰጥተውታል ። ለነፍሳቸው ደኅንነትም እንደ መልካም አባት ያስብላቸው ስለነበረ ፍቅሩ ተሰምቶአቸው "አቡነ" ብለውታል ። እንደ እስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ሥርዐት ግን ቄሱ አቡነ ሲባል ጳጳሱ አምባ (አባ) ይባላል ። ለምእመናን ከጳጳሱ ይልቅ ቄሱ ይቀርባልና ከሣቴ ብርሃን ሰላማም በፍጹም ትሕትና ሁልጊዜ ከምእመናን ጋር የቅርብ ግንኙነት ያደርግ ነበርና አምባ በማለት ፈንታ አቡነ ብለውታል ።በአፍሪካ ውስጥ ታላላቅ መምህራን የነበሩባቸው ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ሲጠፉ በኢትዮጵያ የተቋቋመችው ቤተ ክርስቲያን ግን ማንኛውንም ችግር አልፋ እስከ ዛሬ በመቆየትዋ ወንጌልንም አጽንታ በመገኘትዋ ከብፁዕ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን የተቀበለችው ብርሃነ ትምህርትዋንም ሳታጨልም በመኖርዋ ለመጀመሪያ ሐዋርያዋ ለአቡነ ሰላማ የትጋቱና የፍቅር አገልግሎቱ ፍሬ መሆንዋ ሲያስደንቅ ይኖራል።ስ.ጽ.ብ.







የወንጌልን ብርሃን በኢትዮጵያ ያበራው ብፁዕ ሰላማ

## በአቡነ ሰላማ ጊዜ የተፈጸሙ ልዩ ልዩ ድርጊቶች

### 1-መካሪ ( አበ ነፍስ)

በሕዝቡ የኑሮ አቀማመጥ ይዞታ እ ለመመቸት በአቡነ ሰላማ ጊዜ ብዙ ጥሩ ነገሮች ተደርገዋል ። ከእነዚህም አንዱ በየቀበሌው አንዳንድ ቄስ መካሪ እንዲሆን መደረጉ ነው ። ይህም መጻሕፍትን አንብቦ ለማይጠቀም ሕዝብ ቀርቶ ለዐዋቂና ለተማረም የሚጠቅም መልካም ድርጊት ነበረ ። ይሁን እንጂ በጊዜ ብዛት መካሪው ቄስ ስለ ነ፡ስ ጉዳይ የአባት ያህል ይመክራልና አበ ነፍስ የነፍስ አባት ተብሎ ይጠራ ጀመረ በኋላም ስለ ኃጢአት ኑዛዜ በመቀበል ንስሐ ስለሚሰጥ የንስሐ አባት ተባለ ። እስካሁንም ይህ አጠራር ተጠብቆ ይገኛል ።

### 2- አበ ልጅ (የክርስትና አባት)

አበ ልጅ ማለት የሚጠመቀውን ሕፃን በእግዚአብሔር መንገድ እየመራ እንዲያስተምረው እንደ ዋስ ወይም እንደ ተያዥ ሆኖ በቤተ ክርስቲያን ፊት መቀበሉን የሚያረጋግጥ ምእመን ነው ። ይህ ባህል ከመጀመሪያዋ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጋር አብሮ ተመሥርቶአል ። በጊዜ ብዛት ግን መንፈሳዊ ሥርዐቱን ለቆ የወገን ማደርጃ ሆኖአል ። ከዚህም የተነሣ የሥጋ ዝምድና ያህል ትርጓሜ እየተሰጠው በጋብቻም ላለመቀራረብ ትውልድን በሚመለከት ሁኔታ ተይዞ ይኖራል ።

### 3ኛ/ ቅዱሳት መጻሕፍት

በአቡነ ሰላማ ጊዜ ቅዱሳት መጻሕፍት ከግሪክ (ከሰብዓ ሊቃውንት) መጽሐፍ ወደ ግዕዝ ተተርጉመዋል ። አቡነ ሰላማ ለኢትዮጵያ ካበረከተው ታላላቅ ሥራዎች አንደኛው ቅዱሳት መጻሕፍትን መተርጐሙ ነው ። ነገር ግን አንዳንድ ታሪክ ጸሐፊዎች ቅዱሳት መጻሕፍት ከሰላማ በኋላ በተሰዐቱ ቅዱሳን ወደ ግእዝ እንደ ተተረጐሙ ይተርካሉ ። ይሁን እንጂ ብዙዎች ሊቃውንት ደግሞ ይህ ታሪክ ልክ አለመሆኑን ይናገራሉ (ኪ.ወ.ክ. መዝገበ ቃላት ገጽ 18) የትርጉሙ ሥራ የተከናወነው በአቡነ ሰላማ ብቻ ሳይሆን ግእዝና ግሪክ በሚያውቁ በኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ጭምር መሆኑ አይካድም ። ከአቡነ ሰላማ ጋር ቅዱሳት መጻሕፍትን ወደ ግእዝ የተረጐሙ የኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ስም አለመታወቁ ትውልደ ክርስቲያንን እጅግ አሳዝኖአል ። ያም ሆነ ይህ የሰባ ሊቃውንት ትርጉም በአቡነ ሰላማ ጊዜ መተርጐሙ በብዙ መንገድ ተረጋግጦአል ምክንያቱም ከሰላማ እስከ ዘጠኙ ቅዱሳን ድረስ አንድ መቶ ዘመን ሲሆን እስከዚያ ድረስ ቤተ ክርስቲያንዋ ያለ መጽሐፍ ኖረች ማለት አይቻልምና ።

### 4ኛ/ ቋንቋ

የጥንቱ ግእዝ፦ ዛሬ እንደምናነበው ከካዕብ እስከ ሳብዕ ያለው ድምፅ በፊደሉ አልነበረም ። ግን ግእዙን ብቻ አናጋሪ አድርጎ ይነበብ ነበር ለምሳሌ "ሐወለተ አከሰመ" ሓውልተ አክሱም ማለት ነው በዚህ ሁኔታ ቅዱሳት መጻሕፍትን ለመተርጐም አስቸጋሪ ስለሆነበት አቡነ ሰላማ ከኢትዮጵያ ብሔራውያን ሊቃውንት ጋር ተመካክሮ በጥንታዊው የፊደል ቅርጽ መሠረት ከካዕብ እስከ ሳብዕ ያለውን ትእምርተ ድምፅ (ዋየል) አዘጋጀ ከዚህ በኋላ፦ ቅዱሳት መጻሕፍትን የሃይማኖት ቅዋንቅዋ ከሆኑት ከዕብራይስጥና ከግሪክ ሳይርቅ ተርጉሞ ጸፈበት ።

ወደ ገጽ ፲፱ ይዞረል





www.ethiopianorthodox.org

# የሴቶች ዓምድ

አዘጋጅ ብርሃን ተድላ

## ሲቶች በወንጌል መምህርነት

ሴቶች ዛሬ በሰለጠነው ዓለም ሳይሆን ቀደም ብሎ እንኳ በማስተማር ችሎታቸው የተመሰከረላቸው መሆኑን ከታላቁ መጽሐፍ ልንረዳ እንችላለን ።

ይኸውም ለማስረጃ ያህል ጥቂቶችን ብንጠቅስ እሥራኤልን ያዳነው ሙሴ ታሪክንና ጠቅላላውን ትምህርት የተማረው ከእናቱ ከዮካብድ እንደነበር ለማወቅ ተችሎአል ።

የሥዕለት ልጅ የነበረው ቅን ዳኛ እየተባለ የሚነገርለት ሣሙኤልም የተማረው ከእናቱ ከሃና እንደነበር ከታሪክ እንማራለን እንደዚሁም መጥምቁ ዮሐንስም ከእናቱ ከኤልሳቤጥ እንደተማረ ከመጽሐፍት ልንረዳ እንችላለን ።ሊቁ ዮሐንስ አፈወርቅም ቢሆን መምህሩ እናቱ እንደነበረች ከታሪክ እንረዳለን። እንግዲህ እነዚህን ለምሳሌ ጠቀስን እንጂ ብዙዎች ሊቃውንት ከእናታቸው እንደተማሩ ታሪክ ይመሰክራል ።

አዎን እነዚህ ከወንጌል መምህራን አልተማሩምልትሉ ይሆናል ።ነገርግን እነዚህ የጠቀስናቸው እናቶች መንፈሳዊያንና ሃይማኖተ ጽኑዎች የጸሎትና የሃይማኖት ሴቶች እንደነበሩ መጽሐፉ ራሱ ያብራራል ።

ከዚህም ሌላ በሐዋርያት ሥራ በም. 18 ቁ 24 ላይ እንደተጻፈው ሴቶች ያላመኑትን በማስተማር እንዳሳመኑ እንረዳለን ።

በጠቅላላ ሴቶች የማስተማር ዘዴና ብልሃት ስለሚችሉ እንኳንስ ያላመኑትንና ህፃናትን ማስተማር ቀርቶ ሊቃውንትን እንኳ አስተምረው ማሳመን የሚችሉ ጥበበኞች መሆናቸው ተረጋግጦላቸዋል ።

በተለይ ሴቶች ህፃናትን የመማረክ ዘዴ ስለሚችሉ ህፃናትን ወንዶች ከሚያስተምሩአቸው ይልቅ ሴቶች ቢያስተምሩአቸው ጥሩ ውጤት የሚያስገኝ መሆኑን ከላይ በጠቀስናቸውና እነርሱን በመሳሰሉ ሴቶች ስለተረጋገጠ ዛሬ በሰለጠኑት አለማት የሕፃናት መምህራን በጠቅላላ ሴቶች ሆነው እናገኛቸዋለን።

በሃገራችንም ቢሆን ባሉን የሕፃናት ማዋያ ት ቤቶች የሚያስተምሩት ሴቶ



ወ ት ንብረት አበበ በማስተማር ላይ ሳለች

ች እንጂ ወንዶች አይደሉም ።

በቤተ ክርስቲያናችንም ብዙ ወጣት ሴቶች በላቸው የዕረፍት ጊዜ በበጎ ፈቃዳቸው በየእሑድ ት/ቤቶች በመዘዋወር ሕፃናትና ወጣቶችን የሰንበት ትምህርት እያስተማሩ ናቸው ። እርግጥ ጥቂቶቹ ለመንንዣ የሚሆን እየተከፈላቸው የሚያስተምሩ እንዳሉ ከወጣቶች መምሪያ ጠይቀን ተረድተናል እ ብዛኞቹ ግን በነፃ ያገኘነውን በነፃ እናካፍላለን በማለት በፈቃዳቸው

በመዘዋወር ማስተማራቸውን የወጣቶች መምሪያ እንደሚያውቀውና እንደሚያመሰግናቸው ገልጾልናል ። ይህን መሠረት በማድረግ በዛሬው ጽሑፋችን በአዲስ አበባ ከተማ ከሚገኙት የወንጌል መምህራት ጥቂቶቹን አግኝተን የወንጌል ትምህርት የት እንደተማሩና እንዴት እንደ ሚያስተምሩ በዚሁ ሥራቸውም ምን ችግር እንደገጠማቸው ጠይቀናቸው የሰጡንን ሃሳብ አቅርበንላችኋል ።

ይህን አገልግሎት ለመጀመር ያነሳሳኝ ሰው ሳይሆን እራሴ ነኝ ቢሆንም እስከዚያ ድረስ ሴቶች ስላልተሰማሩበት ለመጠየቅ እንኳ ብዙ ጊዜ በመፍራት ቀርቼ ነበር ። በኋላ ግን በጊዜው የነበሩትን የመምሪያ ኃላፊ ለፈተና ለመቅረብ እችል እንደሆነ ጠይቄአቸው እንደምችል ስለነገሩኝ ከሌሎች ጋር ለፈተና ቀረብሁ ፈተናውን ካለፍኩ በኋላ ግን እኔ ሳልሆን የፈተናው አዘጋጅ ኮሚቴ ችግር ገጥሞት ነበር ። ምክንያቱም እስካሁን ያሉት የሰንበት መምህራን ወንዶች እንጂ ከሴቶች ስለሌሉ በቀጥታ እንዳስተምር ብላክ በእኔም ሆነ በመምሪያው ወይም በሚመለከተው ክፍል ችግር ይገጥማል ተብሎ ስለታሰበ ፈተናውን ማለፌ እንዳለ ሆኖ ቢጋዜጦች እንዲተችበት አንዳንድ ሰዎች እንዲወያዩበት ቅዱስ ሲኖዶሱ በመጀመሪያ ተወያይቶእንዲያምንበት ስለሚያስፈልግ ከእኔ ጋር የነበሩ ወዲያውኑ ሲመደቡ እኔ ግን የሴት ወንጌላውያት እስካሁን ስላልተሰማሩ እንድቆይ ተደርጌ ነበር ። በኋላ ግን ከላይ የተጠቀሱት ክፍሎች ተወያይተውበትና ተችተውበት ከጨረሱ በኋላ ለማስተማር እንድምችል ተነገረኝና ቀጠልኩ ።

የጀመርኩትም በ1970 ዓ.ም.ውስጥ ነው አሁን ምስት ዓመቱ ነው ።

ከብዙ ጊዜ ጀምሬ መንፈሳዊ ትምህርቶችን እከታተላለሁ በዚያም ተመስጦ ስላለኝ ትምህርቱን ከሚሰጡት መምህራኖች መካከል ጥሩ የአሰባበክ ዘዴ ያላቸውን ስለማተኩርበት እንደነሱ ማስተማር እመኝ ነበር ። ከዚያ ነው ብዙ ጊዜ ለማስተማር የተዘጋጀሁት በተለይ ግን በቅድስት ሥላሴ ካቴድራል አዘጋጅነት ለሁለት ወራት ያህል በሰበታ ጌተ ሰማኒ ገዳም ኰርስ ተዘጋጅቶ በነበረበት ጊዜ ከትምህርቱ አንዱና ዋናው "የስብከት ዘዴ" ነበር ። ስለዚህ በዚያን ጊዜ ነው የበለጠ እራሴን ያዘጋጀሁት እኔ የተማርኩት ግን ባለሁበት ማኅበርና በየጊዜው በሚደረጉት ኮርሶች ላይ በመካፈልና ልዩ ልዩ መጽሐፍችን በማንበብ ነው ።

እኔ በፊትም ሆነ አሁን ሳስተምር ምንም ያጋጠመኝ ችግር የለም ወደፊትም የሚያጋጥመኝ አይመስለኝም እንዲያውም ሴቶች ሲያስተምሩ ተደማጭነት በሚሄዱበት ጊዜም ተቀባይነት አላቸው እኔም በተመደብኩበትም ሆነ ተጋብዤ በማስተምርበት በደስታ ትምህርቱን ከሚከተሉኝ በስተቀር ያጋጠመኝ ችግር የለም ።

በቤተ ክርስቲያን አካባቢ ያሉ እህቶችየክርስቶስም ሆነየቤ ክርስቲያንፍ



ወ ት የልፍ ዓለም ተስፋዬ

ቅር አቃጥሏቸው በሚናገሩበት ጊዜእልፎ አልፎ ሀሜት ሽሙጥሚ —— ወዘተ ሊኖር ይችላል ። ግን ያንን ሁሉ መታገስና በቆራጠኝነት እስከ መጨረሻው መቀጠል መልካም ውጤት ያስገኛል ።

የሴቶች በጉባዔ መካከል መስበክ ቀርቶ መሰብሰብን እንደነውር የሚቆጥሩ ሰዎች በነበሩበት በአንድ ጉባዔ ላይ ሀሳብ ለመስጠት ተነስቼ ከጭንቀትና ከፍርሃት ብዛት ምንም ሳልናገር ቁጭ ያልኩበትን ጊዜ አስታውሳለሁ። አንዳንዶም ሴቶች በቤ/ክርስቲያን ውስጥ ምንም ድርሻ እንደሌላቸው አድርጌ ከመገመቴ የተነሳ ተስፋ እቆርጥ ነበር ። ሆኖም ተስፋ በቆረጥኩበትም ሆነ በሌላ ጊዜ ከጐኔ ሆነው ያበረታቱኝና በእግዚአብሔር ቃል ኮትኩተው ካሳደጉኝ ውስጥ መምህር በላይ መርሻና መምህር መንክር መኰንን አልረሳቸውም

አሁን የእግዚአብሔር ክብሩ ይስፋና ያለምንም ጭንቀትና ፍርሀት በወንዶችም ሆነ በሴቶች መካከል ስለክርስቶስም ሆነ ስለ ቤ. ክርስቲያን ሀሳቤን ሙሉ በሙሉ መግለፅ እችላለሁ ታዲያ አሁን ያለኝን ሁኔታ ለመያዝ የቻልኩት ከብዙ ጊዜ ልምምድ በኋላ ነው ።

በዚህ አጋጣሚ ለኢ/ኦ/ተ/ቤ/ተከታታይ ሴቶች የማስተላልፈው ቢኖርም ንም እንኳ አንዳንድ ችግሮች አልፎ አልፎ ቢኖሩም ያለምንም ተስፋ መቁረጥና መሰልቸት ፣ ከሥርዐትና ከእምነት ባልወጣ ሁኔታ በአንድ ላይ ሆነው የስብከትን ዘዴም ሆነ ስለ ቤ/ክ/ አንዳንድ ጉዳዮችን በመወያየት ለቤ/ክርስቲያን ያላቸውን ድርሻ ከማበርከት እንዳይቆጠቡ ነው ።



ወ/ት ቤተ ልሑም

በእግዚአብሔር ፈቃድ የቤተ ክርስቲያን ስብሰባዎች መሳተፍ ከጀመርኩኝ ወዲህ ያለኝን ያህል ለሕፃናት ለማካፈል ምኞት ስለነበረኝ ይህን በሥራ ለመተር ጉጉ ሞክሬአለሁ ።

በመንፈሳዊ አገልግሎት ሥመራ ብዙውን ጊዜ የማሳልፈው በዕውቀት ጥልቀት ካላቸው አባቶች ትምህርት በመውሰድ ሲሆን ያለችኝን ጥቂት ለማካፈል የሞከርኩበት ጊዜ በጣም አጭር ነው ።

መቸም አምላካችን የዓለም መድኃኒት ክርስቶስ ሲያስተምር አይሁዳዊ ወይም የግሪክ ሰው የለም፣ባሪያ ወይም ጨዋ ሰው የለም ወንድም ሴትም የለም ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁና ገላትያ 3፣28 ባለው ቃል መሠረት ይህን ልንጀምር ችለናል ።

ለዚህ የተቀደሰ አገልግሎት ቅንብር ያነሳሳኝ የመጀመሪያው እግዚአብሔር ሲሆን በተጨማሪም ክርሱ ሥር ሆነው የሚገኙ በቤተ ክህነት የወጣቶች ጉዳይ መምሪያና በመንፈሳዊያን መሪዎች ኃላፊነት ነው ።

በዚህም ላይ እስካሁን ድረስ በሄድሁበት ስፍራ ሁሉ ለራሴ የሚጠቅመኝን መንፈሳዊ እውቀት ከመሰብሰብና በመንፈሳዊ ሀሳብ ከመደጋገፍ በስተቀር በእግዚአብሔር ኃይል ምንም ችግር እንዳልገጠመኝ ስገልጽ መንፈሳዊ ደስታ እየተሰማኝ ነው ።

ከዚህ ቀጥዬ የምሰጠው አስተያየት

ወደ ገጽ ፲፫ ዞሯል







www.ethiopianorthodox.org

# ቅዱስ ጋብቻ



አቶ ሙሉጌታና መምህርት አበባየሁ ጋብቻቸውን በፈጸሙበት ጊዜ

ጋብቻ በአምላክ የተፈቀደ ባል ለሚስት ሚስት ለባል በመተሳሰብ ኑሮን በትክል ለመምራት የተወሰነ ቅዱስ ሕግ ነው ።

ይሁን እንጂ ዛሬ በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ስለጋብቻ ሕግና ሥርዓት ጽፎ ለማስረዳት ሣይሆን ሚያዝያ 12 ቀን 1972 ዓ ም. ጋብቻቸውን በቤተክርስቲያን ሥርዓት ስለፈጸሙት ሁለቱ ወጣቶች ቅዱስ ጋብቻ ሁኔታ እንጽፋለን ። አቶ ሙሉጌታ መለሰ ከዚህ ቀደም የሃይማኖተ አበው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ቅርንጫፍ ማኅበር በደብረ ማርቆስ ከተማ በተክለ ሃይማኖት ት/ቤት ወንጌላዊ ተግባሩን ያካሂድ በነበረበት ወቅት ክርስቲያናዊ ድርሻውን ሲያበረክት የነበረና አሁንም በማገልገል ላይ የሚገኝ ነው ።

ይህ ብቻ ሳይሆን ስለታሪካዊትና ጥንታዊት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲን ሕልውናና ደህንነት የሚያስብና የሚደግፍ ፍጹም ክርስቲያን ነው ። እንዲሁም መምህርት አበባየሁ ዘውዱ በክርስትና ዓላማዋ የጸናችና ከራሷ አልፋ ተርፋ ለሌሎች ክርስቲያን ወጣቶች ክርስቲያናዊ አቋማቸውን እንዲያጠናክሩ በመምከርና በማስረዳት ታላቅ ተሳትፎ ያበረከተች እህት ናት ።

መጽሐፍ ቅዱስ በትንሹ የታመነ ደግሞ በብዙ የታመነ ነው ። በማለት እንደሚያስረዳው ፤ ሁለቱ ወጣቶች የፈጸሙት አኩሪና ቅዱስ የሆነ የተክሊልና የቁርባን ጋብቻ ለብዙ ወጣቶች የተራራ ላይ መብራት በመሆን ታላቅ ኦርቶዶክሳዊ የሆነ ትምህርትን እንደሚሰጥ እናምናለን ።

እንደዚሁም የሥልጣኔ አዳራሽ የሆነች የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፤ ልጆቿ በአምላካዊ ቃል ትእዛዝ መሠረት ሕግና ሥርዓቱን በመጠበቅና ለሌሎችም ወጣቶች ፋና ተብርሃን በመሆናቸውና ጸንተው በመገኘታቸው ደስ ልትሰኝ ይገባታል ።

ሁለቱ ተጋቢዎች የብርቱካን ዛፍ የሚያፈራ ብርቱካን ነውና የቤተ ክርስቲያንና የወላጆቻቸውን ሕግና ሥርዓት በመከተል እነሆ ክርስቲያናዊ የኑሮ ቤታቸውን አስተማማኝ በሆነ በእምነት አለት ላይ መሥርተዋል መሠረቱም ጽኑ ነውና ታላቅ ውሽንፍር ሊነቀንቀውና ሊያውከው አይችልም ።

## ሰላማ ....

ከገጽ ፱ የዞረ

### 5ኛ/ የሃይማኖት ትምህርት

ከሣቴ ብርሃን ሰላማ ያመጣልን ትምህርተ ሃይማኖት በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የተመሠረተው በሐዋርያት የተሰበከውና በ325 ዓ.ም. በ318 ኦርቶዶክሳውያን ሊቃውንት የጸናው ትምህርተ ሃይማኖት ነው ። በሚያስተምርበት ጊዜ፡- ከኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ጋር በመወያየት ለትምህርተ ሃይማኖት ልዩ ልዩ ሥረዮችን(ተርምኖሎጂዎችን) አዘጋጅቷል ። ለምሳሌ በግሪኩ ሰርስኪያ የሚለውን በግእዝ ሃይማኖት ፒስቲስ እምነት ትርያዶስ ሥላሴ በማለት የመሳሰሉትን ሥረዮች በትክክል ተርጉሞአል ።

ብፁዕ አቡነ ሰላማ በእግዚአብሔር ፈቃድ ለኢትዮጵያ ቤ ክርስቲያን ሐዋርያ ከመሆኑም ጋር ብዙ በረከቶችን ስለአስገኘላት በዓመት ሁለት ጊዜ ሐምሌ 26 እና ታሕሣሥ 18 ቀን ቅዱስ አባት ብላ ታከብረዋለች በስሙም ቤተ ክርስቲያን አንጻለች በትግራይ ሀገረ ስብከት ብቻ በአቡነ ሰላማ ስም የታነጹ 3 አብያተ ክርስቲያናት አሉ ።

ከሣቴ ብርሃን ሰላማ ለኢትዮጵያ ቤ ክርስቲያን ቀዳማዊ ሐዋርያ መሆኑ በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ ደረጃ ታውቋል ። ስለዚህም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ይህን ታላቅ መምህር፡- "አባ ሰላማ ከሠተ ለነ ብርሃነ ዜናሁ ለመድኅኒነ" አባ ሰላማ ብርሃን የሆነ መድኃኒታችንን ዜና ገለጠልን እያለች የወንጌል መልእክተኛነቱን ትመሰክራለች ።

# የሃይማኖት ዐምድ

«ዓለሞች ሁሉ በእግዚአብሔር ቃል እንደ ተዘጋጁ ፤ ስለዚህም የሚታየው ነገር ከሚታዩት እንዳልሆነ በእምነት እናስተውላለን» (ዕብ. ፲፩፡፫) ።

## ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን

የክርስትናን ሃይማኖት ፍጹም ተስፋ አጉልቶ የሚያሳይ የምሥጢራት ጉልላት ከሞት በኋላ የሚገኘው የአዲስ ሕይወት ትንሣኤ ነው ።

በመሠረቱም ሕይወት የሚገኘው ከሕይወት እንደመሆኑ የክርስቶስ ሕያውነት ለአማኞችም አዲስ ሕይወትን የሚሰጥ መሆኑ ተጽፎአል ። ይህም በቃል የሚነበብና የሚተረጐም ብቻ ሳይሆን በተግባርም የተገለጠ መሆኑን ከታሪክ ማኅደር መገንዘብ ይቻላል ።ከሞት በኋላ ሕይወት ስለመኖሩ ፤ ወይም ሙታን እንደሚነሡ የሚነገር የክርስትና ሃይማኖት መመሪያ በሆኑት ቅዱሳት መጻሕፍት ብቻ ሳይሆን በሌሎችም ከክርስትና ሃይማኖት በመለስ በመላው ዓለም አሉ ከሚባሉት ሃይማኖቶች የአብዛኛዎቹ መመሪያዎች በግልጥ ያስረዳሉ ።ለምሳሌ የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች የሆኑ ሁሉ ስለ ትንሣኤ ሙታን ወይም ከሞት በኋላ ስለሚኖረው ሕይወት በሰፊው የሚናገር መመሪያ አላቸው ።

ቀደም ብሎ በተሰጠው ሕገ ኦሪት ከሚያምኑ አይሁዳውያንም አብዛኛዎቹ በተለይ ፈሪሳውያን በሚል የሃይማኖት ስመ ነገድ የሚጠሩት ክፍሎች መንፈስ መላእክትና ከሞት በኋላም ሕይወት መመኖሩን የሚያምኑ ሲሆኑ "ሰዱቃውያን" በሚል ሥያሜ የሚጠሩት ወገኖች ግን ይህ ሁሉ መኖሩን የሚክዱ እንደነበሩ ቅዱስ ሉቃስ በጻፈው የሐዋ.ሥራ 23.8-9 ባለው ክፍል መመልከት ይቻላል ።

እንግዲህ በዚህ ዓይነት ሊኖር የሚችለው ሁለት ዓይነት አመለካከት የመላውን ዓለም ሕዝቦች ከሁለት በመክፈል አብዛኛው ስለሙታን ትንሣኤ ሲያምኑ ሌሎች (መለስተኛ ብዛት ያላቸው) ይህን የአዲስ ሕይወት ተስፋ በመጠራጠር ከመካድ የሚደርሱ አሉ ። ስለዚህም ይላል ሐዋርያው ጳውሎስ ሙታን እንደሚነሡ ካላመንን እምነታችን ወይም ክርስቶስ ከሞት ተነሥቷል ብለን ማመናችን ከንቱ ነው ። ሙታን የማይነሡ ከሆነ እንደሰው በኤፌሶን ከአውሬ ጋር መታገሌ ምን ይጠቅመኛል? አንተ ሞኝ አንተ የምትዘራው የስንዴ ቅንጣት እንኳ መሬት ላይ ወድቆ ካልሞተ ሕይወት አያገኝም 1ኛ ቆሮ. 15.12-57 ።

ቀደም ካለው የብሉይ ኪዳን ታሪክ እንደምንረዳው ሞት ሳይነካቸው በቀጥታ ከሥጋዊ ሕይወት ወደዘለዓለማዊ ሕይወት የተሸጋገሩ አሉ ። ለማስረጃም ያህል ፤

1ኛ ከአበው ነቢያት አንዱ ሔኖክ የተባለው የእግዚአብሔር ሰው መልካም አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር በማድረጉ ከነሕይወቱ እንደተሠወረ በዘፍጥረት 5. 24 እና በዕብራውያን 11.5 ተመልክቷል ።

2ኛ ነቢዩ ኤልያስ በእሳት ሠረገላ በሕይወት እንዳረገ ተጽፎአል ፤ 2. ነገ.2፡1-14 ።

በሌሎችም ነቢያት አድሮ መንፈስ ቅዱስ ስለሙታን ትንሣኤ ያናገረው ተስፋ እጅግ ብዙ ነው ለምሳሌም በትንቢተ ኢሳ. 26፡19 "ሙታንህ ሕያዋን ይሆናሉ ፤ ሬሣቸውም ይነሣል ። በምድር የምትኖሩ ሆይ ይህን ስሙ ጠልህ የብርሃን ጠል ነውና ምድርም ሙታንን ታወጣለችና ንቁ ፤ ዘምሩም" ይላል ።በትንቢተ ሕዝ.37፡10"ትንፋሽም ገባባቸው ሙታንም ሕያዋን ሆኑ እጅግም ታላቅ ሠራዊት ሆነው በእግራቸው ቆሙ የሚል ቃል ይገኛል ።

በትንቢተ ዳንኤል 12.2-4" በምድር ትቢያ ውስጥ በሞት ካንቀላፉት ብዙዎች ይነቃሉ እኩሌቶች ወደዘለዓለም ሕይወት እኩሌቶችም ወደዘላለም ዕፍረትና ጉስቁልና ይሄዳሉ ።

ይህም ማለት ጥበበኞች እንደሰማይ ፀዳል ፤ ብዙ ሰዎችንም ከኃጢአት ወደ ጽድቅ የሚመልሱ እንደከዋክብት ለዘለዓለም ይደምቃሉ የሚል ግልጥ የጽሑፍ ማስረጃ ይገኛል ።

ይህም ሁሉ አባባል ዕውነት መሆኑን የሚያረጋግጥ የክርስቶስ ቃል በቅዱስ ወንጌል "በዚያን ጊዜ ጻድቃን በአባታቸው መንግሥት እንደ ፀሐይ ይበራሉ የሚሰማ ጆሮ ያለው ይስማ»የሚልነው ማቴ. 13 ፤ 43 ይህንም መሠረት በማድረግ ስለሙታን ትንሣኤ በሰፊው ለመገንዘብ በማቴ.25.31-46 ያለውን ብንመለከት ሙታን በአዲስ አካል መነሣታቸውን ብቻ ሳይሆን ከተነሡ በኋላ ሁሉም እንደየሥራቸው በሚቀበሉት ፍርድ እኩሌቶቹ ለዘለዓለም ሕይወት እኩሌቶቹ ደግሞ ለጉስቁልና ወደዘለዓለም ጥፋት መተላለፋቸውን እንደሚገልጥ ያስገነዝባል ። በዚህም የነቢያትና የሐዋርያት ትንቢታዊ ትምህርት የተባበረ ሆኖ በመገኘቱ 318 ሊቃውንት ለመጀመሪያ ጊዜ በንቂያ በተሰበሰቡ ጊዜ ከደነገጉት የሃይማኖት ትምህርት ውሣኔ አንዱ ክፍል ወይም መደምደሚያው በሙታን ትንሣኤ እናምናለን ። የሚመጣውንም ሕይወት ተስፋ እናደርጋለን የሚል ሆኖ ይገኛል ። ይቀጥላል ።

ቁ መክብብ አጥናው





www.ethiopianorthodox.org

# ይህን ያውቁ ኖሯል ?

እጅጉ ረታ ።

በብሉይ ኪዳን በተለይ ደግሞ በኦሪት ዘፍጥረት ስለተገለጠው የዓለም አፈጣጠር ሁኔታና ስለ ቀደሙ አባቶች ታሪክ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በአንዳንድ ምሑራን አካባቢ ጥርጣሬ አሳድሮ እንደ ነበር ይታወቃል ።'

ዛሬ ግን በታላቁ መጽሐፍ የተነገሩትን ታሪኮች ወይም የተፈጸሙ ድርጊቶችን በውል የሚያረጋግጡ ማስረጃዎች መገኘታቸውን አፍ ሞልቶ ለመናገር ከሚያስችል ዘመን ላይ ደርሰናል ። ለይስሙላ ካልሆነ በስተቀር ይህን ማንም ሰው ሊያብልና ሊያስተባብል አይችልም ። ዕድሜ ለአርኪዎሎጂ


ለዘመናት በመሬት ተቀብረው ፤ በአሸዋ ተዳፍነው በቆዩት ጥንታውያን የከተማ ፍርስራሾች ላይ ከ19ኛው ምዕተ ዓመት አጋማሽ ጀምሮ በየአቅጣጫው የተከናወነው የቁፋሮ እሰሳ ለአርኪዎሎጂ ምሑራን ከፍ ያለ ድል አስገኝቷል ። ለመጽሐፍ ቅዱስ ትክክለኛነትም ውልፊት የማያደርግ ማስረጃ ለማቅረብ ተችሏል ፡፡

ባለፉት ዓመታት እንዲህ ያለው የአርኪዎሎጂ ምርምርና ጥናት ተካሂዶ ተጨባጭ ማስረጃዎች ከተገኙባቸው ቦታዎች አንዱ ዛሬ ኢራቅ ፤ ጥንት የባቢሎንና የአሦር መንግሥታት የተመሠረቱበት በኤፍራጥስና በጤግሮስ ወንዞች መካከል የሚገኝ ምድር ነው ።

በመሠረቱ የኤፍራጥስ ጤግሮስ ሸለቆና አካባቢው ሲጀመር ፤ ጀምሮ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የተቆራኘ ታሪክ ያለው መሆኑን ራሱ መጽሐፉ ያስረዳል ዘፍ. 2፥ ቁ. 10-15

ባለታሪኮችም የሰው ልጆች በመጀመሪያ መንደር ቆርቁረው ከተማ ከትመው የኖሩበት ወይም ባጭር ቃል ለመግለጥ ሥልጣኔ "ሀ" ተብሎ የበቀለበት ፤ ያቆጠቆጠበት ሥፍራ የኤፍራጥስ ጤግሮስ ሸለቆ እንደነበር ያረጋግጣሉ ። ይህን ለማረጋገጥ በተካሄደው የአርኪዮሎጂ ቁፋሮ ጥናትና ምርምር ከጥፋት ውሃ በፊትና በኋላ የነበሩ እያሌ የከተማ ፍርስራሾችን ለማግኘት ተችልዋል ። ጠቃሚ ማስስረጃዎች ከተገኙባቸው ከተሞች ውስጥ እረዱ ፡ አቡድ፡ኤፈክ፡ዑር፡ኪሽ፡ሲፖር አከርጅ ይገኙባቸዋል ። ካርታውን ይመልከቱ፡

እነዚህ የጥንት ከተሞች በጥላን የተዘጋጁ መንገዶች ያሉዋቸው ባለ ሁለት ሦስት ፎቅ ሕንፃዎች የተሠሩባቸው እንደ ነበሩ የአርኪዎሎጂ ጠበብት አካፋ ዛሬ ግልጥልጥ አድርጐ ሊያሳይ ችሏል ።




በአርኪዎሎጂ ምርመራ ፡ ጥንት ተቆፍረው ፡ ከተገኙ ፡ የጥንት ፡ ከተሞች ፡ በከፊል ፡፡

በዚያን ዘመን 2500 ዓ ከክርስቶስ ልደት በፊት ትምህርት ቤቶች በየከተማው ከመስፋፋታቸው በላይ እያንዳንዱ ት ቤት የራሱ የሆነ የተሟላ ቤተ መጻሕፍት ነበረው ። የዚህ ጽሑፍ አንባቢ በዐይኑ ካላየ ማመኑ እስኪቸግረው ድረስ በየቤተ መጻሕፍቱ የተከማቹት በሸክላ ሰሌዳ ላይ የተዘጋጁ ድሑፎች ወይም የመማሪያ መጻሕፍት ልክ በአሁኑ ዘመን ካሉት የትምህርት መጻሕፍት ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው ነበሩ በዚያን ጊዜ እንደዛሬው ዘመን ሁሉ ፡ በየት ቤቱ ቤተ መጻሕፍት የኢንሳይክሎፔድያ፤ የዲክሽነሪ፤ የቋንቋ፤የሰዋሰው የስነ ጽሑፍ መጻሕፍቶች ነበሩ ። በዚያን ጊዜ ልክ እንደ ዛሬው ዘመን ሁሉ የሕግ ፤ የፖለቲካ ፤ የሃይማኖት የጂኦግራፊ መጻሕፍት ነበሩ ። በዚያን ጊዜ የሳይንስ፤የመድሐኒት የአስትሮኖሚ የአስተሮሎጂ ትምሕርቶች የሚሰጡባቸውም መጻሕፍት ነበሩ ። በአርኪዎሎጂ ምሑራን ትጋትና ጥረት የእነዚህና የሌሎችም ቁሳቁሶች መገኘት በዚያን ዘመን የነበረው የሥልጣኔ ደረጃ ከፍተኛ እንደነበር ያስረዳል ።

ይህንን በሚመለከት ረገድ አንዳንድ በቁጥሩ የተገኙትን አስደናቂ ማስረጃዎችን እንደሚከተለው ባጭር ለማቅረብ እሞክራለሁ ።

1 አርካድ፤ ሌላው ስሟ ሲፖር፡— ከናምሩድ ከተሞች አንዷ ስትሆን የተቆረቆረችው ከአዳም 8ኛ ትውልድ በሆነው በማቱ ሰላ ዘመን ነው ። አርካድ በቤተ መጻሕፍት የከበረች ከተማ ስለነበረች ነበር ሱፓር የተባለ ስም ሊሰጣት የበቃችው ። ሲፓር ማለት ቅሉ በቋንቋቸው "የመጽሐፍ ከተማ" ማለት ነው ። በዚች ቦታ ኖኅ ከጥፋት ውሃ በፊት የተከበሩ መጻሕፍትን በሸክላ ሰሌዳ ገልብጦ /ቀርጾ/ እንደቀበረና ከጥፋት ውሃ በኋላ ቆፍሮ እንዳወጣ ይነገራል ። እነዚህ ጽሑፎች ከእርሱ በፊት የነበሩ የዘመኖችና አበውኒቱታሪክ የሚያወሱ ሳይሆኑ እንደማይቀሩ ይገመታል ።

የዚችን ከተማ ፍራሽ ራሳም በ1888 ዓ.ም. ሲል በ1894 ዓ.ም. አስቆፍረው ባጠቃላይ 60000 የሸክላ ጽሑፍ ሰሌዳዎች ተገኝተዋል ።

2/ በ300 ዓ.ዓ ከልደት በፊት የነበረ አንድ ቢሮሱስ የተባለ የባቢሎን አገር ታሪክ ጸሐፊ ስለኖኅ መጻሕፍት ከዚህ በላይ የተገለጠውን የሚያስረዳ ታሪክ ከማርዶክ ቤተ መቅደስ ቤተ መጻሕፍት ከምችቶች ውስጥ አግኝቶ የመዘገበበት ሰሌዳ በ1029 ዓ.ም በዶክተር ውሊ የሚመራው የአርኪዎሎጂ ቡድን አግኝቶታል ።

3/ ለጋሽ ፤ ከዑር ከተማ 80 ኪሎ ሜትር ላይ ርቃ የምትገኝ ናት በርዜክ የተባለ የአርኮሎጂ ጥናት ባለሙያ ከ1877-1901 ዓ.ም ባደረገው የቁፋሮ ፍለጋ በዚች ከተማ ውስጥ በዘመኑ ተወዳዳሪ ያልተገኘለት አንድ ትልቅ ቤተ መጻሕፍት ለማግኘት ችሏል ።

4/ ካልኔ ፤ /ኒፑር/ ይችም ከናምሩድ ከተሞች አንዷ ስትሆን ዘፍ. 10፥10 ፒተርስ ሔይንስ እና ሒልፕሬች በተባሉ የፔንሲልባንያ ዩንቨርስቲ ምሑራን አማካይነት በተከናወነው የቁፋሮ ፍለጋ ከ1888-1900 ዓ.ም ባለው ጊዜ 50000 የሸክላ ሰሌዳ ጽሑፎች ተቆፍረው ወጥተዋል እነዚህም የሸክላ ጽሑፎች የተጻፉበት ዘመን 3000 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት መሆኑ ተረጋግጧል ። ይህም ዘመኑ ከጥፋት ውሃ በፊት ማለት ነው። ከተገኙት ጽሑፎች ውስጥ 20.000 መጻሕፍት የአንድ ቤተ መጻሕፍት ንብረት ሲሆኑ፤ የቀሩት ግን ልዩ ልዩ የቤተ መንግሥት ሰነዶች ምስክረ መጻሕፍት መዝገበ ቃላት የተጠናቀቁ /ኮምፒሊት ወርክስ/ የሕግ መዛግብት ፤ የሳይንስ ፤ የስነ ጽሑፍና የሃይማኖት ጽሑፎች ሆነው ተገኝተዋል ።

5/ ጀመዲት — ናስር ፤ ይች ከተማ ከጥፋት ውሃ በፊት የነበረች ከተማ ናት ። 3500 ዓመት ከክ . ል .በፊት በእሳት ቃጠሎ ጠፍታለች ። በ1926 ዓ.ም በፊልድ ሙዝየም አክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ አማካይነት በተደረገው የቁፋሮ ፍለጋ ፤ ዶክተር እንግዳን የተባሉ የአርኪዎሎጂ ምሑር ካገኙት አንድ የሸክላ ሰሌዳ ላይ እንደተረዱት የጥንት ባቢሎናውያን አምልኮ በአንድ አምላክ /እግዚአብሔር/ ማመን እንደነበርና ፤ ለጣኦታት መንበርከክ /መገዛት/ የመጣው ከጊዜ በኋላ መሆኑን ገልጸዋል ።

6 ዑር አብርሃም ተወልዶ ያደገባት ከጥፋት ውሃ በፊት የተቆረቆረች ከተማ በ1929 ዓ.ም ዶክተር ሲኤል ውሉ ባደረጉት የቁፋሮ እሰሳ ተገኝታለች ከፍርስራሹ ከተገኙት ጽሑፎች ገሚሱ የሂሳብ ገሚሱየመድኃኒት ፤ ገሚሱ የታሪክ ወዘተ ትምህርት መለማመጃ ሲሆን ሌሎችም አብረው ተገኝተዋል።አብርሃም በዚህ ት ቤት ሳይማር እንዳልቀረ አርኪዎሎጂስቱ ዶክተር ውሉ ያምናሉ አብርሃም በዚያን ዘመን ስመ ጥሩ በሆነች እንዲህ ባለች የሰለጠነች ከተማ ተወልዶ በማደጉ ፤ ከላይ ከኖኅ ፤ ከኖኅ ሴም ሲወርድ ሲዋረድ የተላለፈውን የስነ ፍጥረትና የቀደሙ አባቶች ታሪክ መዝግቦ ለተከታዩ ትውልድ ሳያስተላልፍ እንዳልቀረ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሑራን ይገምታሉ ።

ይህ እርግጥም ሆኖ ከተገኘም በኦሪት ዘፍጥረት የተወሳው የሥነ ፍጥረትና የዘመነ አበው ታሪክ ለሙሴ በቃል ብቻ የተላለፈለት ሳይሆን ፤ በጽሑፍ የቆየው ነው ለማለት ይቻላል ። ይቀጥላል ።

ምስክረ — መጽሐፍ

1/ የመጽ ርዕስ-መጽሐፍ ቅዱስ ሕያው ሲሆን ፤
ደራሲ—ሰር ቻርልስ ማርስተን
ሕትመት—1947 እ . ኤ . አ .

2 የመጽ ርዕስ — በዘመናችን የተደረሰባቸው የሳይንስ ምርምር ውጤቶችና መጽሐፍ ቅዱስ
ደራሲ ኤ.ረንድል ሸርት

3 የመጽ. ርዕስ — የመ. ቅ. መሠረቱ እንዴት ጠንካራ ነው
ደራሲ — ቻርልስ ኤፍ ጂሪገዘ

## ሴቶች በወንጌል .....

ከገጽ ፲፩ የዞረ

ሁላችንም ለመንፈሳዊ ሥራ ለመነሳት የተዘጋጀን እንድንሆን ማለትም እራሳችንን እያሳትን የምንሰማ ብቻ ሳይሆን ሰምተን በሥራ ለመተርጐም እንድን በቃ ከሥጋችንና ከከንቱ መሻቱ ጋር ታላቅ ተጋድሎና ትግል ማድረግ ይኖርብናል ። በተለይም በአንዲት ተዋሕዶ እምነት በቤተ ክርስቲያን ጥላ ሥር እየተሰበሰብን በክርስቶስ ስም ክርስቲያን የተባልን ሁላችን ወደ ፈጣሪያችን ዕለት ዕለት በጾም ፤ በጸሎት ፤ በስግደት እራስን ዝቅ በማድረግ እንድንቀርብና ሕግጋቱን ለመፈጸም እራስችንን ማስለመድ የሥጋችንን ምኞት መኮርኮም በስሙም ለመመስከር የማናፍርና የተዘጋጀን እንድንሆን ሳላሳስብ አላልፍም ።እለሙም ምኞቱም ያልፋሉ የጌታን ፈቃድ የሚያደርግ ግን ለዘላለም ይኖራል ።

እንግዲህ ሐዋርያው ቅ ጳውሎስ ሲያስተምር "ወንጌልን ልሰብክ ተዘጋጅቻለሁ በወንጌል አላፍርምና " ብሎ በሮሜ መልእክቱ ላይ እንደተናገረው ሁሉ እህቴቻችንም የቀደሙትን ቆራጥ ወላጆች ዓርአያ በመከተል በቃሉ ሳያፍሩ ለማስተማር እንደተዘጋጁና በማስተማር ላይ እንዳሉ ገልጸውልናል ።እኛም የእነዚህን እህቶች አርአያ በመከተል ስለ እግዚአብሔር እውነተኛውን ነገር ለመረዳት በሐሰት ትምህርትና በሰዎች ወሬ ሳንታለል መጽሐፍ ቅዱስ በማጥናት እውነትን እራሳችን እንፈልግ ሌሎችንም እናስተምር ማንም ቢደብቀው የእግዚአብሔር ቃል ተደብቆ ስለማይቀር ሰው በሚችለው አቅሙ የተወሰነለት እድሜ ሳታልቅበት ፈጣሪውን ማገልገል ግዴታው ነውና ።

ብርሃን ተድላ



www.ethiopianorthodox.org

# ምን እንርዳዎ ?

ይህ ዓምድ አንባቢዎች ችግራቸውን የሚገልጹበት ፣ ለችግራቸው መፍትሔ የሚሰጡበት ፣ ጥያቄና መልስ የሚያቀርቡበት ስለሆነ ምን እንርዳዎ ተብሎ ተሰይሟል ።




አዘጋጅ ተስፋ ጥሩነህ

ስልክ ቍጥር 11-66-16

የፖ.ሣ.ቁ. 31-37

አዲስ አበባ


ለትንሣኤ መጽሔት የምን እንርዳዎ
ዐምድ አዘጋጅ
አዲስ አበባ

አስራ ሁለተኛ ክፍል ጨርሼአለሁ እድሜዬም 21 ዓመት ነው ታዲያ በዚህ መሐል እንዳለሁ ማለት የስምንተኛ ክፍል ሣለሁ አንድ ወጣት ለወደፊቱ የትዳር ጓደኛው እንድሆን ጠየቀኝ እኔም በፍፁም እንደማልፈልገውና በአሁኑ ዕድሜዬና ጊዜዬ የትምህርት ፍቅር እንጂ ተደራቢ ሌላ ፍቅር ለመያዝ እንደማልፈልግ በደንብ ገለፅኩለት ። ይህ በእንዲህ እንዳለ እኔም እንደ ወንድሜ ሳየው እሱም ምንም አይነት ሃሣብ ሳያነሣብኝ ለተወሰኑ ዓመታት ቆየን ታዲያ በመሐል ይህ ወጣት ለትምህርት ወደ ውጭ አገር ሄዶ ደብዳቤም ይፅፍልኛል እኔም እፅፍለታለሁ አሁን በሚፅፍልኝ ጊዜ አሁንም ከኔጋር ያለው የትዳር ስሜት እንዳለቀቀው ተስፋ ባለመቁረጥ እስከ አሁን እንደጠበቀ እድሜሽ እየገፋ ሲሄድ ታስቢበታለሽ በማለት ነው ስለዚህ ምን አለበት እሺ ብትይኝ ፀባዬንም ለተወሰነ ጊዜ ታውቂዋለሽ በማለት ይፅፍልኛል እኔግን እስከ አሁን ድረስ ምንም የእሺ.ታ.መልስ አልሰጠሁም ከሱም በፊት ሆነ ከሱ በኋላ ወይንም እርሱን እራሱን የወንድ ጓደኛ ያደረግሁት ሰው የለም ለምን ቢባል ወንዶችን ለመቅረብ በጣም ስለምፈራ እንጂ እስከ መጨረሻው ያለጋብቻ ለመኖር አስቤ አይደለም እሱንም በፀባዩ አልጠላውም ግን ተደራራቢ ደብዳቤዎችን ሲፅፍልኝ በመጨነቅ ይህ ልጅ እውነተኛ ሊሆን ይችላል ይህንን ያህል ዓመት ያረሳኝ በሚል ሃሣብ እየተዋጥኩኝ ሳለሁ በመሐል ይህ ወጣት የኔ የቅርብ ጓደኛ የነበረችውን ወጣት ቃል ተግባብተውና ለተወሰኑ ጊዜያት አብረው እንደቆዩ ከራሱዋ ከልጅቷና ከሌላም ደንበኛ ማስረጃ ባለው ሁኔታ ላውቅ ቻልኩኝ ይህንንም በማስመርኮዝ ብጠይቀው (በደብዳቤ)ም ንም ስለዚህ ነገር እንደማያውቅ ምንም አይነት ነገር ያለመደረጉን ጻፈልኝ ታዲያ ይህን ለምን አደረገ ማለቴ ሣይሆን እኔን በተስፋ ሲጠብቅ ከኖረ ለምን በመሐል ሌላ የትዳር ጓደኛ ጠየቀ 2ኛ/ እኔ ይህንን ልጅ እሺ ብለው ወይንም ወደፊት ብንጋባ በመሐላችን መተማመን ሊኖር ይችላል? 3ኛ/ ይህቺ ይዞአት የነበረችው ወጣት በአሁኑ ሰዓት በትዳር ዓለም የምትገኝ ስለሆነ ነገሩ ባጣ ቆይኝ መስሎኛል ምን ትመክረኛለህ? 4ኛ ወጣቱ ልጅቷን በመያዙ አልተቃወምኩም ምክንያቱም አልፈልግህም ብዬ ስለነበረ አሁን እኔን ከፈለገ ከአሁን በፊት የነበረውን ለምን ደበቀኝ? በደብዳቤ በፍጥነት መልስ እንድሰጠው ቃል ሊያስገባኝ በመሞከር ላይ ስለሚገኝ በወጣትነቴ ችኩዬ መልስ ከመስጠቴ በፊት ምክራችሁን ለግሡኝ እኔም ሆነ እሱ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን አማኞች ነን ።
ቢቻል ስሜን ደብቅልኝ

ስምሽን ደብቄልሻለሁ

ጥያቄሽን ተመልክቸዋለሁኝ አዎ ለጊዜው ሊያስጨንቅሽና ለመወሰንም ያቅትሽ ይሆናል ። ይሁንና እንደጠየቅሽው ይህ ሰው በመጀመሪያ ያንችን ማንነት አጥንቶ በክብር መጠየቁንና አንችም መልሰሽ ላስብበት ሳይሆን ጭራሽ አልፈልግህም እንዳልሽው በመሐሉም ይህ ወጣት ያንቺ የቅርብ ጓደኛ ከነበረችው ወጣት ጋር ቃል ተግባብተውና ለተወሰኑ ጊዜያት አብረው እንደቆዩ ከራስዋ ከልጅቷና ከሌላም ደንበኛ ማስረጃ ባለው ሁኔታ ልታውቂ እንደቻልሽ እርሱ ግን በደብዳቤ ብትጠይቂው እንደካደሽ ገልጸሻል ። ያንቺ ችግር እንደገለጽሽው ለምን እኔን ከጠየቀ በኋላ በመሐል ሌላ የትዳር ጓደኛ ጠየቀ? ማለት መሆኑንም በተጨማሪ ጠቁመሻል

እንግዲህ የኔ መልስ ከላይ እንደገለጽኩት ይህ ወጣት በክብር ሲጠይቅሽ አንቺ እኮ ላጥናህ ፣ ጊዜ ስጠኝ ፣ ላስብበት ከአእምሮየም ሆነ ከሰው ጋር ልመካከርበት ብለሽ መልሰሽ አልጠየቅሽውም በጭራሽ አልፈልግም ብለሽ አሰናብተሽዋል ። ስለዚህ ይህ ሰው አንቺ እንዳልሽው ጓደኛሽን ጠየቀ ይህም ሊሆን የቻለው ካንቺ ተስፋ ስላጣ ከጥሩ ጋር የዋለ ጥሩ ነው በማለት ሊሆን ይችላል ያችኛዋን የጠየቀው እንግዲህ እንደኔ አስተያየት የግድ የትዳር ጓደኛን መምረጥ ስላለበት ካንቺ ተስፋ ስላጣ ሌላዋን ቢጠይቅ ምንም የሚያስነውር ሥራ አልሰራም እላለሁ ።

በሁለተኛው ጥያቄሽ ብንጋባ አሁን ስጠይቀው ስላላመነ አለመተማመን ሊኖር አይችልም ወይ? ስላልሽው በእውነት በሁለት ተጋቢዎች መካከል ከመጋባታቸው በፊት አለመተማመን ካለ ከተጋቡ በኋላ ይወገዳል ለማለት ያስቸግራል ። ይሁን እንጂ አለ መተማመን መልክ አለው ይህም አንቺ እንዳልሽው በወሬ አለመተማመንና በዓይን አይቶ አለመተማመን ነው ።

በወሬ ሰምቶ አለመተማመን ለምሳሌ ያንቺ ጓደኛሽ "ጠይቆኝ ነበር" ብላ የነገረችሽ ዓይነት ነው ። አዎ ጓደኛ ጥሩ ነው አንዳንዴ ደግሞ ጥሩ ጓደኛ ካልሆነ ምቀኛ ነው ይህ የሚጠይቅሽ ሰው የተማረ ጥሩ ሰው መሆኑን ከተረዳች መጥፎ ጓደኛ እንኳንስ ጠይቆኝ ነበር ሌላም ስለ እርሱ መጥፎ ወሬ ታወራለች እንዲህም የሚያደርጉ መጥፎ ጓደኞች ብቻ ሳይሆኑ አንቺ ጥሩ እድል እንዳይገጥምሽ የሚፈልጉ ምቀኞች በአፋቸው ግን ወዳጆችሽ መስለው የሚታዩ ሁሉ ናቸው እንዲያውም አንችንስ ጠይቆኝ ነበር ነው ያለችሽ ሌሎቹንማ ከዚህ የባሰ መጥፎ ወሬ ፈጥረው የሚያወሩባቸው ብዙዎች ናቸው ከዚህም ሌላ ይህ ሰው ድንገት እንኳን አድርጐት እንደሆን አሁን በደብዳቤ ስትጠይቂው በደንብ አብራርቶ ሊያስረዳሽ ስለማይችል አዎን ብል እሽ አትለኝም በሚል አስተሳሰብ ሊሆን ይችላል ። ስለዚህ የዚህ ሰው ጥፋት ይህ ብቻ ሆኖ በሌላው ጠባዩ ተስማሚሽ ከሆነ በግል አስተያየቴ ይህ የፈተና መውደቂያ ሊሆን አይችልም ።

እህት እንደኔ ምክር ከሆነስ ምርጫሽን የምትመሠርችው አንች ባልሽው በዚህ በጥቃቅኑ ነገር ሳይሆን በመጀመሪያ በእውነተኛ ፍቅር ላይ መሆንና በተቻለ መጠንም በዕድሜ እኩያሽ በጠባይም ተመሳሳይሽ በዕውቀትም ረገድ ደረጃችሁ ተመጣጣኝ ወይም ብዙ ያልተራራቀና ሊቀራረብ የሚችል ቢሆን ለሁለታችሁም ስሜት ደስ የሚያሰኝ ይሆናል ። ጠባይ ለጠባይም የምትቻቻሉና የምትግባቡ መሆናችሁን ደህና አድርገሽ መረዳት አለብሽ ።

የኑሮ ጓደኛሽን ለማግኘት ረጋ ባለ መንፈስና እጅግም ባለመጣደፍ ባለመራቅና ባለመቅረብም በዕድሜ ተስተካካይ በባሕርይም ተመሳሳይ መሆን አለባችሁ ግን በእድሜ እንኳ በመጠኑ ብትበላለጡ ምንም አይደለም ። በዚህም ላይ ጠለቅ ብለሽ ማስተዋልና መመራመር አለብሽ ማስተዋልም ስልሽ በቅርብ ተጠግቶ በሩቅም ፈንጠር ብሎ ሳይሆን አካባቢውን ጭምር በመመልከት ነው ። በተቻለሽ መጠንም ምን ያህል የመግባባት መንፈስ እንደሚኖራችሁ እያንዳንዳችሁ ለትዳር የሚመጥን ዐመል እንዳላችሁ ጥናት ማድረግና ወደ ሚዛናዊ ግምት ለመድረስ የሚያስችለውን ሁኔታ ሁሉ ተከታትለሽ ማወቅ ግዴታሽ ይመስለኛል ።

ከዚህም ሌላ አንዲት ወጣት የወደፊቱን የኑሮ ዕድሏን በአንድ ወንድ ላይ ልትመሠርት ስታስብ አስቀድማ ጠባይ ለጠባይ መግባባታቸውንና መቻቻላቸውን ማወቅ ለሁለቱም ይጠቅማቸዋል ። ለምሳሌ ደንቆሮና ዕውር ቢገናኙ ምንም ሳይነጋገሩ ወይም ሳይደማመጡ እንደሚለያዩ ሁሉ ሁለታችሁም በጠባይ ባትስማሙና ባትግባቡ አንዳችሁ እንደ እውር አንዳችሁ እንደ ደንቆሮ ሆናችሁ ሳትግባቡ እንደምትለያዩ አትጠራጠሪ ። ስለዚህ ጋብቻ የሚመሠረተው ጠባይ ለጠባይ በመግባባት ሐሳብ ለሃሳብ በመቃረብ መሆኑን መረዳት አለብሽ ።

ሌላው ደግሞ የሃይማኖት ጉዳይ ነው ከሁለት የተለያየ ሃይማኖት የሚጋቡ ባልና ሚስት እጅግም በትዳራቸው መሐል ሰላም አይኖርም ብዙዎች ሃሳብ ለሐሳብ ለመለዋወጥና መንገድ የሚያገኙት ከልክ የሚቀራረቡትም በሃይማኖት በኩል ያላቸው ዝንባሌ አንድ ሆኖ ሲገኝ ነው ። ስለዚህ በሃይማኖት ጉዳይ ችግር እንደሌለባችሁ በአንዲት በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ክርስቲያን ውስጥ መሆናችሁን ገልጠሻል በተረፈ በአሉባልታ ወሬ አትሸበሪ ክርስቲያንም ስለሆንሽ ስለዚሁ ጉዳይ መልስ ከመስጠትሽ በፊት ጸልይበት ከዚያም መልሱን ታገኛለሽ መልካም ባል የጸሎት መልስ ነውና ።

ጥያቄሽን የጋብቻ አማካሪ ከሆኑት ከወ/ሮ ብርሃን ተድላ ጋር ተወያይተንበታል ።

# ከሚሠሩ ጋር ዕውቀታችሁን አስተባብሩ

በዚህ ዓለም ተግተውና ተባብረው ከሚሠሩ ሠራተኞች አንዱን ክፍል የያዙ ዕውቀታቸውንም አስተባብረው የሚሠሩ መናንያን መነኮሳት መሆናቸውን ተሪክ ያስረዳል ። የእነዚህም ክፍል እጅግ ሰፊ የሆነ ታሪክ ያለው ነው ። ሁኖም በአጭሩ የእነዚህ ሥራና ዓላማ መሠረቱ በፍጥረቶች ሁሉ ዘንድ ደኅንነት ፣ ሰላም ፣ ኅብረት ሰፍነው እንዲኖር በእውነት የሚጸልዩ ናቸው ፣ በአንዳንድ ክፍል እንደሚታየውና እንደሚሰማውም ወገንን ጐሣን ቋንቋን ተከትለው ልዩነት አይፈጥሩም ዓላማቸው የተመሠረተበት ከዚህ ቀደም በትንሣኤ መጽሔት ቁጥር 18 የገዳማት አመሠራረት እንዴት ነው ? በሚል ርዕስ በሰፊው የተጻፈ ስለሆነ አልፌ እኔ ያየኋቸውን በዘመናችን ከነበሩ እውነተኞች አበው አጭር ታሪክ አቀርባለሁ ። ከእነዚህም አንዱ አባ ወልደ ማርያም መርሻ ናቸው እኚህም መናኝ አባት ትጉህና በተለይ እውነተኛውን ነገር ብቻ ተከትለው ጥቃት ስለሚደርስበት ወገናቸው ተቆርቋሪ የሀገራቸውንም ታሪክ አክባሪ ነበሩ ። በዚህም መሠረታዊ የሆነ ዓላማቸው አባ ወልደ ማርያም መርሻ በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ገዳም ሲኖሩ አባ ወልደ ማርያም ዓፀደ ይባሉ ነበር ። ይህም የተጠሩበት ስም ታላቅ ታሪክ ያዘለ ነው ። ምክንያቱም አባ ወልደ ማርያም ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ አስበው ከተወለዱበትና ከአደጉበት ሀገር .




www.ethiopianorthodox.org

ከጐጃም ጉንድ ልሜት ጊዮርጊስ ከተባለው ቦታ ተነስተው አዲስ አበባ ሲገቡ በመንፈሳዊነት አቀባበል ከሁሉም በልጠው የተቀበሏቸው ወይዘሮ ዓፀደ ገለሜናቸው ። እኚህም የቅድስና ደጋፊና ተካፋይ የሆኑ ወ/ሮ አባ ወልደ ማርያምን ተቀብለው ከአስተናገዱ በኋላ የምናኔ ሐሳባቸው ከግቡ እንዲደርስ ወደ ኢየሩሳሌም እንዲገቡ ያበቋቸው የቅድስና ተግባር እጅግ አስደሳች የሆነ ዓላማ ነው ለማለት እንችላለን ። እነዚህ የተጠቀሱትም የቅድስናና የርኅራኄ ሥራ ሠሪዎች ዓላማቸው እንደጥንታውያኑ መናንያን አበው እጅግ የጠነከረ ስለሆነ አባ ወልደ ማርያምም በበኩላቸው ለእኚህ ወ/ሮ የሚከፍሉት ውለታ በጸሎት ብቻ ማሰብ ለሕሊናቸው በቂ ሁኖ ስላልተሰማው ራሳቸውን እንደመንፈሳዊ ልጅ መድበው አባ ወልደማርያም ዓፀደ እንዲባሉ በመወሰናቸው ነው ። ይህም ወይዘሮ ዓፀደን በመንፈሳዊ ሥራቸው እንደ አባትም እንደ እናትም የሚያስቆጥር የደግነት ሥራ መፈጸማቸውን የሚያስረዳላቸው ቀዋሚ ምስክር ነው ። ከዚህ ላይ ጥንታውያን የኢትዮጵያውያን ታሪክ በምዕመናንና በመናንያን መካከል የነበረ የተቀደሰ ዓላማ የጐሣ ልዩነትን የሚያስከትል መሆኑን ተረዳን ።

አባ ወልደማርያም መርሻ አድርባይ



አባ ወ/ማርያም መርሻ እኚህ ነበሩ

ነትን ጠባይ ፈጽመው ከሀሊናቸው ያስወገዱ መናኝ አባት ነበሩ ። አባ ወልደ ማርያም መርሻ በይበልጥ እንዲመሰገኑ የሚያደርጋቸው ተግባር በኢየሩሳሌም የጠቅላላ ኢትዮጵያውያን ገዳም ገብተው በመርዳት ብዙ ዘመን ያገለገሉና ከጥንት የነበረውንም የአበው ታሪክ ጠንቅቀው እየተከታተሉ ያጠኑ እውነተኛ መናኝ ናቸው ። ይህም አንዳንድ ግብዞች የራሳቸውን መብትና ታሪክ ዝቅ አድርገው ግብጾች አባቶቻችንናቸው እያሉ ከሚያስቱ ሰነፎች ሳይተባበሩ ኢትዮጵያውያንን አስረጅ ከአበው የተነገራቸውን ሁሉ ሳይጠራጠሩ እውነተኛ ነገር እንደሆነ አምነው አንድ በአንድ ለይተው ሲያስጠኑኝ የነበሩ አባት ናቸው ። ከገዳሙ ማስረጃ በመጥፋቱም የተነሣ ብዙ ችግር ነበር ይህም ችግር ከ1838 ዓ.ም. ጀምሮ የነበረውንና የሆነውን የሚያስረዱ ሰነዶች በእሳት ተቃጥለው ጠፍተው ነበር ሁኖም በአባ ወልደማርያምና ሌሎቹም ተግተው ስለ ሀገራቸው በሚያገለግሉ ረዳቶች ጭምር ሰነዶቹን ከዋናው መዝገብ እየቀዳን ስንሰበስብ ያን ያህል ዕንቅፋት ፈጣሪዎችም አንዳንድ ሰነፎች እንደ ነበሩ አልዘነጋውም ።ይህም በሥራዬ ላይ የቋንቋ ርዳታ እንዲረዱኝ ያቆምኩትን ሰው በውስጣችን ባሉ ሰነፎች ጠቋሚነትና ተባባሪነት ግብጾች በገንዘብ ገዝተውት እኔ የሰበሰብኩትን የማስረጃዎቻን ኮፒ 28 ገጽና ከአባ ወልደ ማርያም ቤትም የተቀመጡትን ሁለት ታላላቅ የታሪክ መጻሕፍት ወስዶ አስረከባቸው ። ብዙ ገንዘብም በሥራው ምክንያት ወስደውብኝ ነበርና የአባ ወልደማርያም ፍጹም መናኝነትና አባትነት በዚህ ጊዜ ትልቅ ሥራ ሠራ ይህም ሥራ እኔ አብረውኝ ስለሀገራችን መሥራት የሚገባቸው ሰዎች በውሳጣችን ሁነው የጠላት ደጋፊዎች በመሆን በብዙ ድካም የሰበሰብኩትን ሰነድ ለግብጾች እንዲረዳቸው አሳልፈው ከሰጡ ልልቀቅላቸው ብዬ ተናድጄ ወደ ማርዕባ የሚባል የመጨረሻ በረሃ የሆነ ገዳም ለመሄድ እንደ ተነሣሁ አባ ወልደማርያም በጥንቃቄ ያስቀመጡትን መዝገብ በመውሰዱ አዘኑ አለቀሱም ግን ፍጹም ናቸውና ራሳቸውን አጽናንተው እኔን ከተነሣሁበት ሐሳብ ለማስቀረት ታላቅ ተአምራታዊ ሥራ ሠሩ ይህም ሁኔታ እንዲት ኢትዮጵያዊት ያገቡ ጠበቃ ነበሩና ሂደው ነገሩን በማስረዳት የተወሰደብንን በሕግ በማስመለስ ከሕግ ጠበቃው ቤተሰቦች ጋር መጥተው እኔንም አጽናንተው ነገሩን ሁሉ እንዳስረዳቸው ጠይቀውኝ አንድ በአንድ ከአስረዳኋቸው በኋላ በአባ ወልደማርያም ብርታትና በሌሎቹም ገዳማውያን ኀዘን ተረድቼ ከተጽናናሁ ወዲህ ከላይ እንደተጠቀሰው አታላዩን በፍርድ ቤት ከሰው የወሰደውን አስረጅ ኮፒ 28 ገጽ አስመልሰው ከወሰደውም ገንዘብ 49 ፓውንድ ከ80 ሣንቲም በፍርድ አስገድደው ቅጣቱን ተቀብሎ ገንዘቡን እንዲከፍል አስፈረዱበት ። የፋይሉም ቁጥር 3592 በ1952 ዓ.ም. በ16 1ኛ ወር ይገኛል ቁጥሩ በፈረንጅ ዓመት ነው አባ ወልደ ማርያም መርሻ በተጠቀሰው ገዳም እውነተኛ የመናኝነት አገልግሎታቸውን እያበረከቱ ግብጾችን የምንረታባቸውን እውነተኞች ሰነዶች ሰብስበው በእጃችን እንደገቡ በዓይናቸው አይተው በመደሰት ሰነዶቹ በጥንቃቄ እንዲቀመጡ አጥብቀው እያስረዱ ቆይተዋል ። እንዲሁም ግብጾች በሃይማኖት አባትነት ምክንያት ገብተው የሰፈሩበትን የኢትዮጵያውያን አጽመ ርስት የሆነ መልሰን እጅ ለማድረግ የሚያስችሉንን ሰነዶች በማየታቸው ተደስተዋል ግን ቢደሰቱም በግብጾች መነኮሳት ግፈኝነት እያዘኑ አባ ወልደ ማርያም መርሻ ከመናኝነታቸው ሳይዛቡ በ1946 ዓ.ም. ጥር 10 ቀን ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ ። አሁን የምጠይቀው የግብፅ መነኮሳት ከሚበድሉን በደል ያላነሰ የሚጐዱን በአጭሩ ከላይ እንደገለጽኩት ሁሉ በውስጣችን የሚገኙ አንዳንድ አስመሳዮች ስለሆኑ ታርመው እንደ አባ ወልደ ማርያም ለሀገራቸው እውነተኛ አገልግሎት ያበርከቱ እላለሁ ።እውነት ይለምልም አስመሳይ ይታረም ። ጥያቄ ያለው ይጠይቅ ።

መምህር ኪዳነ ማርያም ገ ሕይወት



# የጤና ዐምድ

## የጨጓራ በሽታ

የጨጓራ በሽታ በየትኛውም ሀገር በየትኛውም ዕድሜ የሚገኝ ፆታና ወገንን የማይለይ አደገኛ በሽታ ነው ። በተለይም ፔፕቲክ አልሠር በዓመት ከ10-12 በመቶ የሚሆነውን የሰው ዘር እንደሚለክፍ ሲገመት በጠቅላላው በዓለም ውስጥ ወደ ሆስፒታል ከሚገቡት 2 በመቶ ሰዎች በዚሁ በሽታ ጠንቅ እንደ ሆነ ተረጋግጧል ። የጨጓራ በሽታ (ፔፕቲክ አልሠር) ዓይነቱ ሁለት ሲሆን ይኸውም ዲወዲናል አልሠር ከ20 - 50 ዕድሜ ክልል ውስጥ በጣም አይሎ ሲታይ ጋስትሪክ አልሠር ከ45 - 55 ዕድሜ ክልል ውስጥ በብዛት ይታያል።

## የጨጓራ በሽታ ምንድነው ? መነሻውስ?

የጨጓራ በሽታ በመሠረቱ የስቶማክ (ሆድዕቃ) ና የዲወዲነም (ትንሹ የአንጀት ክፍል መነሻ) ግድግዳ መገሸለጥ ፣ መላላጥ ብሎም መቁሰል ሲሆን ይኸውም አሲድና ሌላም ነገር ላለው የሆድ ዕቃ ፈሳሽ ክፉኛ ከመጋለጡ የተነሳ ነው ።

በድንገት አልኮል ያለባቸው መጠጦች በብዛት መጠጣትና አንዳንድ መድኃኒቶችን (አስፒሪን ፣ ቡታዘሊዲን ፣ ስቴሮይድና የመሳሰሉትን) ያለልክ መዋጥ የሆድ ዕቃ ግድግዳ መገሸለጥን ያስከትላሉ ከዚህ የተነሳ በሽተኞች በአደገኛ ሕመም ፣ በደም ማስታወክና በሆድ ዕቃ መቀደድ ጭምር ወደ ሆስፒታል ሊመጡ ይችላሉ ። ለእነዚህ በሽተኞች በቂ የሕክምና ርዳታ ከተደረገላቸውና ለደወፊትም ምክንያት ከሆኑት ነገሮች ከተወገዱ ፈጽመው ይድናሉ ፣ ሆኖም ከነዚሁ ውስጥ አንዳንዶቹ ጋስትሪክ አልሠር የተባለው የጨጓራ በሽታ ሊይዛቸው ይችላል ።

እስከዛሬ ድረስ በተደረገው ጥናት የፔፕቲክ አልሠር ዕድገት አመጣጥና አካሄድ ይታወቅ እንጂ መነሾውን ግን በውል ለማወቅ አልተቻለም ። አንዳንዶች የቤተሰብ ታሪክ በመመርመርና በማጥናት ከዘር ወደዘር መተላለፉን ለማስረዳት ሲሞክሩ ሌሎች ደግሞ በሰው ልጅ በኑሮው በሕይወቱበሚደርስበት ጭንቀትና ብስጭት የተነሳ ነው ይላሉ ። እንደርሰን የተባለ ሰው ፔፕቲክ አልሠር ምን እንደሆነ ሲያስረዳ "ፔፕቲክ አልሠር በሆድዕቃ ውስጥ የሚገኝ ቀዳዳ ነው ። በዚህ ቀዳዳም ባልየው ከሚስቱ ጭቅጭቅና ንዝንዝ ቀስ ብሎ ሾልኮ ያመልጥበታል ብሏል ። ያም ሆነ ይህ የሆድዕቃ ፈሳሽ ውጤት መጨመርና የሆድዕቃንና የትንሹ አንጀትን (ዲወዲነም) ግድግዳ የማቁሰሉ ጉዳይ መሠረታዊ ነው ። የሆድ ዕቃ ፈሳሽ ውጤት ለምን ይጨምራል ? መልሱ ተለይቶ አይታወቅም ። በሌላ በኩል ደግሞ የሆድ ዕቃው ፈሳሽ ውጤት ትክክለኛ ወይም ያነሰ ሆኖ የሆድ እቃው ግድግዳ ግን የመቋቋም ኃይሉ በመድከሙ ለዚሁ ፈሳሽ በመጋለጥ ይቆስላል ። ይህም ሌላው መሠረታዊ ምክንያት ነው ። የሆድዕቃው ግድግዳ የመቋቋም ኃይሉ ለምን ደከመ ቢባል መልሱ አሁንም ተለይቶ አይታወቅም ነው ። እንግዲህ ፔፕቲክ አልሠር በሆድ ዕቃ ፈሳሽ ውጤት መጨመር ወይም የሆድዕቃ ግድግዳ የመቋቋም ኃይል መድከም ሊመጣ ይችላል ማለት ነው።

በእንግሊዝና በአሜሪካ ይህ በሽታ በኃላፊነት ላይ በተቀመጡ ፣ በንግድ ሰዎች ዘወትር በሚጨነቁና በሚያቅማሙ ሰዎች ላይ በብዛት ይታያል ።

## የጨጓራ በሽታ ምልክቶች

የጨጓራ በሽታ ያለበት ሰው ሆድ ዕቃው አካባቢ ይወጋዋል ፣ ያቃጥለዋል ሕመሙም ወደደረቱና ወደጐኑ ወደ ጀርባውም ይሰማዋል ። ያቅረኛል ያቅለሸልሸኛል ይላል ። ወተትሲጠጣ ምግብ ሲበላና ለዚህ በሽታ የተዘጋጁትን መድኃኒቶች ሲጠጣ ሕመሙ ወዲያውኑ ይተወዋል ። ሕመሙ እንደ በጀመረው ጊዜ ከምግብ በፊት ከምግብ በኋላ ሰዓት እየለየ በጊዜው ይሰማዋል፡ ለጥቂት ሳምንታት ይቆይና ፈጽሞ ደግሞ ይሻለዋል እንደገና ደግሞ ከጥቂት ሳምንታት ወይም ወራት በኋላ ይነሳል። ሕመሙ በሚሰማው ጊዜ በሽተኛው ምግብ መብላት ስለማይደፍር ክብደቱ በየጊዜው ይቀንሳል ። ከብዙ ወራትና ከጥቂት ዓመታት በኋላ ሕመሙ እየፀና ሲሄድ ሌሎች ምልክቶች ይታያሉ። ለምሳሌ ያህል ፣ ሀ/ ወደትንሹ አንጀት የሚወስደው በር ሲጠብ በሽተኛው ትውከት ያስቸግረዋል ወደላይ ወደላይ እያለው የተብላላና የኮመጠጠ የሚሸትና ያልተፈጨ ከአንድና ሁለት ቀን በፊት የተበላ ምግብ ያስታውከዋል ሆዱን ይነፋዋል ። የምግብ ፍላጐቱ ይጠፋል ። ክብደቱ በጣም ይቀንሳል። ለ/ የሆድዕቃው ወይም ዲወዲነሙ ሲደማ በሽተኛው ደም ያስታውከዋል ወይ ደግሞ ቀስ በቀስ ሆድዕቃው ውስጥ እየደማ የዓይነ ምድሩ መልክ ከሰል እስኪመስል መጥቆር ይጀምራል ። መድማቱ ካላቆመ በሽተኛው ድካም ድካም ይለዋል ፣ ያልበዋል ፣ መተንፈስ ያስቸግረዋል ፣ ራሱን ያመዋል ያወራጨዋል በጠቅላላው የደሙ ግፊት መጠን ዝቅተኛ ስለሚሆን በአስቸኳይ ወደ ሆስፒታል ገብቶ ደም ወይም ሌላ ፈሳሽ ካልተተካለት ሕይወቱ ከሞት ደጃፍ ላይ ትሆናለች ።

የጨጓራ በሽታን የሚያባብሱት ምክንያቶች ፣ የተለያዩ ቢሆኑም ከብዙ በጥቂቱ ቅመማ ቅመም የበዛበት ምግብ መብላት ፣ በርበሬ የበዛበት ምግብ መብላት ፣ የኮመጠጡ ምግቦች መብላት

ወደ ገጽ ፳፩ ዞሯል ፡



www.ethiopianorthodox.org



# የምእመናን ድምፅ

ይህ አምድ የኢትዮጵያ ኦ.ተ.ቤተ ክርስቲያን በአስተዳደር ተሐድሶ የምትራመድበትና የምትሻሻልበት ክ. ስቲያኖች ስለ ቤተ ክርስቲያናቸው በቀና መንፈስ አስተያየት የሚያቀርቡበት ነው ። በዚህ ዓምድ ሊቀርቡ የሚገባቸው ጽሑፎች የቤተ ክርስቲያናችን ውሳኔዎች ሳይሆኑ የግለሰቦች አስተያየት መሆናቸውን የዓምዱ ተከታታዮች በቅድሚያ እንዲያውቁልን እንፈልጋለን ።

አዘጋጅ ነቅዓ ጥበብ ወንድም የስልክ ቁጥር 11-66-16 የመልእክት ሣ.ቁ. 3137 አዲስ አበባ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በተለይ በአዲስ አበባና በአንዳንድ ከፍተኛ ከተማዎች የመቃብር ቦታ ያላቸው አብያተ ክርስቲያናት በመቃብር ቦታ ብዙ ችግር እንደሌለባቸው ግልጥ ነው ግን የመቃብር ቦታ የሌላቸው አብያተ ክርስቲያናት ምእመናን የመቃብር ቦታ ወደአላቸው አብያተ ክርስቲያናት ሰው በሞተ ጊዜ አስከሬን ይዘው ሲሄዱ አናስቀብርም የሚሉ ለምን ይሆን ? ምክንያቱም ቤተ ክርስቲያን አንዲት ስለሆነች ልዩነት መፍጠር አይገባምና ነው ።

በአሁኑና ባለፈው ዝግጅታችን የመቃብር ቦታ ካላቸው ሁለት አብያተ ክርስቲያናት አስተዳዳሪዎች ጠይቀን ያገኘነውን መልስ ለዓምዳችን ተከታታዮች ማቅረባችን ይታወሳል ።

ይሁን እንጂ በአንድ አቅጣጫ ትኩረት ማድረግ ለአንባብያን መፍትሔ ስለማይሆን የመቃብር ቦታ ከሌላቸው አብያተ ክርስቲያናት መካከል የመንበረ መንግሥት ቅዱስ ገብርኤልን አስተዳዳሪ ፀባቴ ተክለሚካኤል ፈንታሁንን ጠይቀን ያገኘነውን መልስ አቅርበናል ።

<u>የምእመናን ድምፅ</u> ፀባቴ ተክለ ሚካኤል ፈንታሁን የመቃብር ቦታ ያላቸው አብያተ ክርስቲያናት ምእመናን የመቃብር ቦታ የሌላቸው ምእመናን ለቀብር አስከሬን ይዘው ሲመጡ ገንዘብ ክፈሉ ይላሉ የሚል ሐሜት አለ በእናንተ በኩልስ እንዴት ነው ።

<u>ፀባቴ ተክለ ሚካኤል</u> ፈንታሁን ፣ የመቃብር ቦታ ብዙ ችግር ፈጥሮአል ከቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ጽ ቤት ጥቅምት 20 ቀን 1972 ዓ.ም በቁጥር 6 15 72 ተወስኖ ኅዳር 18 ቀን በመሸኛ ደብዳቤ የተወሰነ ገንዘብ እንዲከፈል ባይከፈል የምናስከፍል መሆኑን እንገልጻለን የሚል ደብዳቤ ተላልፎ ምእመናኑን ስለአስቀየመ ውዝግብ አስነስቶ ነበር ።

<u>የምእመናን ድምፅ</u> ፣ ምናልባት ገንዘብ የሚጠይቁት የሰበካ ጉባኤን ደንብ ያሟሉት ነው ወይስ ያላሟሉትን ?

<u>ፀባቴ</u> ፣ እነርሱ የሚሉት ለዘበኞች ነው ግን እኛ ለዘበኛ አንከፍልም ጥበቃም ከአስፈለገ የእኛ ዘበኞች በተራቸው ሊጠብቁ ይችላሉ ለዕዳቱ አጠባበቅ ከሆነም የእኛን ሰበካ ጉባኤ ምእመናን ሊመለከት አይችልም ከዚህም ሌላ የሰበካ ጉባኤን ደንብ ባለሟሟላት እቀበራለሁ የሚል ምእመን ካለ እኛ እንቆጣጠራለን ።

<u>የምእመናን ድምፅ</u> ፣ በእናንተና በቅድስት ሥላሴ ካቴድራል መካከል ስለዚሁ ጉዳይ የተቋቋመ ኮሚቴ አለ ይባላል ከአለስ ምን ውጤት አስገኝቷል ?

<u>ፀባቴ</u> ፣ መቋቋሙን ተቋቁሟል ውጤት ያስገኘ አይመስለኝም ውጤት ቢያስገኝ እስከ አሁን ድረስ ለእኛ ይገለጽ ነበር ። መቼም ችግሩ የምእመናን በመሆኑ ለወደፊቱ አንድ መፍትሔ ሳይገኝለት አይቀርም እላለሁ ።

<u>የምእመናን ድምፅ</u> ፣ ምንም እንኳ የመቃብር ቦታን ባይመለከትም ሁኔታው ከዚህ ጋር የተያያዘ በመሆኑ ለመጠየቅ የፈለግሁት ^^ ፍትሐት ጉዳይ ነው ። ምክንያቱም በአንዳንድ አድባራት ያሉት ካህናት ወደመንደር ሔደን ፍትሐት አንፈታም ላሉ በእናንተስ በኩል ጉዳዩን እንዴት መለከቱት አላችሁ ?

<u>ፀባቴ</u> ፣ የእኛ ካህናት መንደር ሔደው ይፈታሉ በሰበካ ጉባኤ ያልተመዘገቡትን በነፃ አንፈታም ያልተመዘገቡትን የተወሰነ ገንዘብ በሰበካ ጉባኤው ጽ ቤት ደረሰኝ ሰጥተን እንዲፈቱ እናደርጋለን ። እንዲህ ያለውን ሥነ ሥርዓት ለማቋረጥ አይቻልም ሲኖዶሱ ተወያይቶ ይጠቅማል አይጠቅምም የሚል ውሳኔ ሲያስተላልፍ ብቻ ነው ሁሉም አንድ ዓይነት ውሳኔ ሊያገኝየሚችለው፣ ባለፈውና በአሁኑ ዝግጅታችን ከሦስቱ አድባራት አበተዳዳሪዎች ጠይቀን ያገኘነውን መልስ ተመልክተናል ። ታዲያ ቤተ ክርስቲያን አንዲት ስትሆን ምእመናንም አስተዋጽኦና ግልጋሎት የሚሰጡት ለዚህችው እናት ቤተ ክርስቲያን ነው ።

በመሠረቱ እንደዚህ ያለውን ልዩነት የሚፈጥሩት አንንንድ የሰበካ ጉባኤ አባላት መሆናቸውን በአንዳንድ ቦታ ተዘዋውረን ተመልክተናል ። የቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪዎች ሰላም እንዲሰፍንና በምእመናን ላይ ቅሬታ እንዳይኖር ሲጥሩ የምእመናኑ ተወካዮች አባላት ይህ ካልሆነ ከዚህ ደብር





እናስነሣችኋለን ይላሉ ። በዚህ ጊዜ አንዳንዶች ተስማምተው ለመኖር ስለሚፈልጉ ጥፋት መሆኑን እያወቁ ችላ በማለታቸው እንዲህ ያለው ውዝግብ ሊነሣ ይችላል ።

እንግዲህ ለዚህ መፍትሔ የአንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን ጥረት ሳይሆን በአዲስ አበባ ያሉት አድባራትና ገዳማት አስተዳዳሪዎችና ምእመናን ከሚመለከታቸው ባለሥልጣኖች ጋር ተወያይተው አንድ ማዕከላዊ ኮሚቴ ተቋቁሞ ውሳኔ ተሰጥቶበት የሚያከትም ካልሆነ ችግሩ እየተባባሰ እንደሚሔድ ግልጽ ነው ።

ሆኖም ግላዊ አስተያያታችን በሥራ እስከሚተረጐም የሌሎች አድባራትን አስተዳዳሪዎችና ምእመናን ችግር ከማውሳት ሳንቆጠብ በተከታታይ የምናቀርብ መሆኑን እንገልጻለን ።

---

## የጨጓራ..............

ከገጽ ፲፱ የዞረ

አልኮል ነክ መጠጦች መጠጣት ፣ ሻይ ቡናና ኮካኮላ መጠጣት ፣ ሲጋራ ማጤስ አንዳንድ መድኃኒቶችን አስፒሪን ቡታዞሊዲን ፣ ስቲሮይድ የመሳሰሉትን መዋጥ ፣ እረፍትናእንቅልፍ ማጣት መናደድና መጨነቅ መሆናቸውን ብዙ በሽተኞች ያስረዳሉ ።

### <u>የጨጓራ በሽታ የወደፊት ሁኔታው</u>

ምንም እንኳ እየተሻለና እያገረሸ ለብዙ ጊዜያት ቢያንስ ከ5 - 10 ዓመት የሚቆይ ቢሆንም በጨጓራ በሽታ የተለከፉ ሰዎች አብዛኞቹ ከበሽታው ፈጽመው የሚድኑ መሆናቸው የታወቀ ነው ። ከ65 - 70 በመቶ የሚሆኑት በሕክምናና በሚወስዱት ጥንቃቄ ሲድኑ 25 በመቶ የሚሆኑት በሽታው ለሚያስከትለው መጥፎ ሁኔታዎች ባለዕዳ ይሆናሉ ። ቀሪዎቹ 5 - 10 በመቶ የሚሆኑት ደግሞ የቀዶ ጥገና ርዳታ ያስፈልጋቸዋል ። በሽታው የሚያስከትላቸው መጥፎ ሁኔታዎች ፦

1. በሕክምና የማይድንና የማይሽር በየጊዜው የሚነሳ የሆድ ማቃጠልና መውጋት
2. ወደ ትንሹ አንጀት የሚወስደው በር መጥበብ
3. ቁስሉ ሥር እየሰደደ የደም ቧምቧዎችን መጉዳትና እንዲደሙ ማድረግ ፤
4. ቁስሉ ሥር እየሰደደ የሆድዕቃ ሆነ የዲወዲነም ግድግዳ እንዲቀደድ ማድረግ ናቸው ።

### <u>ለጨጓራ በሽታ ሕክምናው ምንድነው?</u>

1/ የኑሮ ሁኔታ ፦

የኑሮ ሁኔታን መለወጥና ከአንዳንድ ልምዶች ራስን መቆጠብ ይህ መቼም ለአንድ ሰው የሚሆንለት ከሆነ አማራጭ የሌለው ሙከራ ነው ። ይኸውም በሥራ ቦታ በትርፍ ጊዜ በቤቱ በኑሮው በአካባቢው ለውጥ ለማድረግ ቢሞክርና በተቻለ መጠንም ሊለወጥ የማይችል ከሆነ ራስን ለነዚህ ነገሮች ብቁ አድርጐ መዘጋጀትና መቋቋም ። አለመጨነቅ አለማቅማማት ሁሉን እንደአመጣጡ ለመመለስ መጣር ። አልኮል ከመጠጣት ሲጋራ ከማጤስ ራስን ፈጽሞ መግታት ።

2. <u>እረፍትና እንቅልፍ</u>

ለትንሽ ጊዜም ቢሆን ወይም ሕመሙ ሊሰማ ሲጀምር ወይም ሊቋቋሙት ከማይችሉት በላይ የሆነ ችግርና ብስጭት ሲያጋጥም ማረፍ ። እፎይ ማለት መልካም እንቅልፍ ደግሞ መተኛት በጣም አስፈላጊ ነው ።

3. <u>ምግብ</u>

ወተት መጠጣት፣ትንሽትንሽ ከ5 - 6 ጊዜያት መብላት ። ከላይ ከተጠቀሱት የምግብ የመጠጥ ዓይነቶች መከልከል ። እጅግም ለምግብ መጠንቀቅ ጭንቀት ስለሚፈጥር ሳይጠራጠሩ መብላት አስፈላጊ ነው ። ይህ መቼም ከበሽተኛ በሽተኛ ይለያያል ። ሆኖም ሕመም በተሰማው ጊዜ ራሱ በሽተኛው ከበላው ምግብ ለወደፊት መጠንቀቅ ይችላል ።

4 በሆድዕቃ ፈሳሽ ውስጥ ያለውን አሲድ ማርከሻ የሚሆኑ የተለያዩ ፀረ አሲዶችን ሕመም በተሰማ ጊዜ ቶሎ ቶሎ መውሰድ ፣ ሕመም እስከሚሻል ድረስ ከሳምንታት እስከ ወራት መወሰድ አለባቸው ።

5/ በብዛት አሲድ ለመፍጠር ወደ ሆድ ዕቃ የሚሄደውን የነርቭ ሥራ የሚፃረር መድኃኒት መዋጥ (አንቲ ኮሉነርጂክስ) የአንጀት ግድግዳ መንቀሳቀስንም ስለሚቀንስ ሕመሙ ይታገሳል ።

6 ለአእምሮ እረፍት የሚሰጥ መድኃኒት መዋጥ ።

እነዚህን ከዚህ በላይ የተጠቀሱትንና የሕክምና ´መድኃኒቶችና ምክሮች ከሀኪም ዘንድ በመሄድ ማግኘት ይቻላል ። በነዚህ መድኃኒቶችና ምክሮች ብቻ በሽተኛው ከተጠቀመ ከብዙ ጊዜያት በኋላ የመዳን ተስፋው እጅግ ከፍተኛ ነው ። በቅድሚያ እንደተገለጸው አብዛኞቹ በዚህ ርዳታ ብቻ ፈጽመው ይድናሉ ። የጨጓራ በሽታ የሚድንና የሚያገረሽ ረጂም ጊዜ የሚወስድ ስለሆነ በሽተኛው እንደተመቸው ከሀኪም ምክርና መድሃኒት ቢያገኝ የተሻለ ነው። ሀኪሙም የበሽታውን ዕድሜ መብዛት የሚያስከትለውንም መጥፎ ውጤት ከበሽተኛው ላይ በመገምገም ሊረዳው ይችላል ። በተጨማሪም በጣም ጥቂት ለሆኑ በሽተኞች የሆድዕቃቸውን ጠቅላላ ሁኔታ ሀ በራጂ በማየት ለ በላስቲክ በማየትና በሌሎችም የምርመራና የላብራቶር መረጃዎች በመደገፍ ቀዶ ጥገና ያስፈልጋቸው አያስፈልጋቸውም እንደሆነ ሀኪሙ ሊገልፅላቸው ይችላል ።

ጥላሁን ተካ





www.ethiopianorthodox.org



# ወጣቶች በቤተ ክርስቲያን

በወጣትነህ ወራት ፈጣሪህን አስብ (መክ. 12-1)

አዘጋጅ ኢሳይያስ ወን
ወንድም አገኘሁ

የወጣቶችን እርምጃ ለመገምገም የሚቻለው በየቤተ ክርስቲያኑ የሚገኙትን የወጣቶች መንፈሳዊ እንቅስቃሴና ጽኑዕ ፍላጐት በማየት ነው ። ይህ ጉዳይ ግልጥ ሊሆን የሚችለው ደግሞ ወጣቶቹ ራሳቸው አስተሳሰባቸውን ፣ ፍላጎታቸውንና እምነታቸውን በንግግርና በሥነ ጽሑፍ ሲገልጡ ነው ። ከዚህም ጋር የሚናገሩትንና የሚያስቡትን ሁሉ በተግባር ሲተረጉሙት ነው ።

በዚህ ትንሣኤ መጽሔታችን ይህ የወጣቶች ዓምድ የምናዘጋጀው ስለመንፈሳዊያን ወጣቶች ያለንን አስተያየት በትምህርት መልክ ለመግለጥና ወጣቶቹ የሚያደርጉት መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ለሌሎች መልካም አርአያ ይሆን ዘንድ ዜናውን በማሰራጨት ትምህርት ለመስጠት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ከመንፈሳውያን ወጣቶች አካባቢ የሚገኘውን ሪፖርትና አስተያየት እያተምን በማውጣት ወጣቶቹ አሳባቸውን እንዲገልጡና መንፈሳዊ ዝንባሌያቸውም እንዲዳብር ለማድረግ ነው ።

ስለዚህ በአሁኑ የወጣቶች ዓምድ ዝግጅታችን በሲዳሞ ክፍለ ሀገር ከአዋሳ ደብረ ምሕረት ቅዱስ ገብርኤል ወጣቶች መካከል ወጣት ወንድሙ አየነው "ወጣቱ ለቤተ ክርስቲያን ያለው ፍቅር" በሚል ርእስ አዘጋጅቶ የላከልን ጽሑፍ ቀጥሎ የተመለከተው ነው።

<u>ወጣቱ ለቤተክርስቲያን ያለው</u> ፍቅር

የሰው ልጅ በምድር ላይ እንዲኖር በአምላካዊ ትእዛዝ ከተፈጠረ ብዙ ዓመታት አልፈዋል ። በርካታ ዘመናት ተቆጥረዋል ።

ሆኖም ስለ ሰብአዊ ፍጡር ሥነ ባህርይም ሆነ ተግባራዊ መዋቅሩ ምጥቀት የሚገልፁ በርካታ መጻሕፍት ቅርፃ ቅርፅ፣ የእምነት ሕግጋት..ወዘተ የመሳሰሉትን ጠቃሚና አኩሪ መዘክርም ሲወርድ ቢዋረድ ጀምሮ ባለው የተፈጥሮ ሕግ መሠረት ሲወራረስ የመጣ ሲሆን ቤተ ክርስቲያንም የዚህ ታሪካዊ ሂደት ተሣታፊ በመሆንዋ ግሩም ታሪክዋንና አስደናቂ ቅርሶችዋን ይዛ እነሆ ላለንበት 20ኛው ክፍለ ዘመን ደርሳለች ። ወደፊትም እስከ ዓለም ፍጻሜ ትኖራለች ።

ጥሩ ታሪክን ፣ ግሩም ሥነ ምግባርንና የማያወላውል ወኔን መልካም አባትና እናት ለተተኪው ትውልድ ማስተላለፍ ከዘመናት መፈራረቅ ልዩ ገጽታ የሌለዉ እንደመሆኑ መጠን በወቅቱ የሚገኘው ክርስቲያናዊ ወጣትም ለተረካቢነቱ አስፈላጊ የሆኑትን መሰናዶዎች በማጠናቀቅ ረገድ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት መንፈሳዊ ዓላማውን በተግባር በመግለፅ ላይ ይገኛል ።

ለቤተ ክርስቲያን መሠረትዋ ክርስቶስ እንደሆነ ሁሉ ሕንጻዎችዋም ካህናትና ምእመናን በመሆናቸው እነሆ ካህናትና ዲያቆናት ሊገኙና መንፈስ ጠንካራ ምእመናን ሊመለመሉ የሚችሉባቸው የወጣት መንፈሳዊያን ማህበራት ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ በቁጥር መጨመር ለቤተ ክርስቲያን ልማትና ለተዋሕዶ እምነት ዕድገት አስተማማኝ ግሥጋሤ ነው ።

ምሳሌም ለመጥቀስ የምወደውና ለዚች አነስተኛ ጽሑፍ ዝግጅት ዓይነተኛ ምክንያት የሆኑትን የሻሸመኔና የአካባቢው የባሌ ዶዶላ ገብረ ክርስቶስና የሲዳሞ ክፍለ ሀገር ወጣት መንፈሳውያን ማህበራት ሐዋርያዊ ተልዕኮና መንፈሳዊ ተሳትፎ ነው ።

ዕዕዋትና አዝርዕት ያለውሃ ሊያብቡና ሊያፈሩ እንደማይችሉ ሁሉ ከቃለ እግዚአብሔር የራቀ የክርስቲያን አእምሮም ከዚህ ያልተለየ ሁኔታ ይታይበታል ። ማለትም ቅጠሉ ያረገፈበት ዛፍን እንደሚመስል አያጠራጥርም ይህንን የተረዱት የወጣት መንፈሳዊያን ማህበራት በአሁኑ ጊዜ የሚያደርጉት ክርስቲያናዊ አስተዋጽዖ አስተማማኝ ምዕራፍ ያለው ነው ።

ወጣቶች በአሁኑ ጊዜ "በጉብዝናህ ወራት ፈጣሪህን አስብ" የሚለውን የመጽሐፍ ቅዱስ አነጋገር በተግባር ከመተርጐማቸውም በላይ የቅድስት ቤተ ክርስቲያንና አንጋፋው ታሪካዊ

ወደ ገጽ ፳፱ ዞሯል



# የልጆች አምድ

'፡ልጆች የእግዚአብሔር ስጦታ ናቸው'
(መዝ 126 ቁጥ 3)

ልጆች ! በዚህ ዓምድ አሁን የተዘጋጀውን በመመልከት በሚቀጥለው ጊዜ ያላችሁን ጥያቄና አስተያየት እንዲሁም ልደታችሁን በምታከብሩበት ጊዜ መልእክታችሁን ከነፎቶአችሁ በመላክና ሀሳባችሁን በማቅረብ የተዘጋጀውንም በመከታተል ብትጠቀሙበት ዓምዱ የእናንተ ይሆናል ።

በዚህ ዝግጅታችን ያቀረብናቸው የአንድ ዓመት በዓሉን ያከበረውን ሕፃን ዮሐንስ ዓለማየሁን 3ኛ ዓመቱን ሚያዝያ ፲ ቀን 1972 ዓ.ም. ያከበረውን ዓለም ባንተ ተስፋንና ከደብረ ጽጌ ቅዱስ ዑራኤል የወጣቶች መ.ማ ተማሪ ኢየሩሳሌም አበበን ነው ።



ሕፃን ዮሐንስ ዓለማየሁ



ሕፃን ዓለምባንተ ተስፋ



ኢየሩሳሌም አበበ

ኢየሩሳሌም ብዬ ያስተዋወቅሁአችሁ ልጅ ግን ከእነዚህ ልጆች ሁሉ በዕድሜዋ ትበልጣለች ስለዚህ እስዋ በደንብ ትነጋገራለች ማለት ነው ፣ እሺ እንግዲህ ለጠየኳት ጥያቄ የሰጠችኝን መልስ አቀርብላችኋለሁ ኢየሩሳሌም ስንት ዓመትሽ ነው ? ስንተኛስ ክፍል ነሽ? 8 ዓመቱ ነው ሁለተኛ ክፍል ነኝ ። መካነ ኢየሱስ ትምህርት ቤት እማራለሁ ።
መጽሐፍ ቅዱስ ታነቢያለሽ ?
ኢየሩስ በት/ ቤት ውስጥ ሁልጊዜ መጽሐፍ ቅዱስ እናነባለን ።
ቅዳሜና እሁድ ደግሞ በዑራኤል የ.ወ. መ.ማ. መጽሐፍ ቅዱስና መዝሙር እማራለሁ ።
ከምታነቢውና ከምትማሪው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ በቃልሽ ያጠናሽውንና ደስ የሚልሽን ጥቅስ ልትነግሪኝ ትችያለሽ ?
ኢየሩስ ፦ አዎ "ህጻናትን ተውአቸው ወደኔ ይመጡ ዘንድ አትከልክሉአቸው መንግሥተ ሰማያት እንደነሱ ላሉ ናትና" (ማር 10 ፣ 14) ሌላ የምታውቂው አለ ? አዎ ብዙ ነው ያጠናሁት "እንደዚህ ያለውን አንድ ህጻን በስሜ የሚቀበል ሁሉ እኔን ይቀበላል" (ማቴ 18፡5)

"እነሆ ልጆች የእግዚአብሔር ስጦታ ናቸው" እንደ ዓለም ባንተ እንደ ያሬድና እንደ ዮሐንስ እንደነሱም ያሉትን ነው መሰለኝ ፡

ኢየሩሳሌም 8 ዓመቱ ነው ብለሻል በዚህ ዕድሜሽ የሠራሻቸውን ነገሮች ታውቂያለሽን ?

አዎ 2ኛ ክፍል ደርሻለሁ ፣ እናቴን በምችለው ሥራ እየረዳኋትና እየተላላኳት ነው ።
ሌላስ ለብቻሽ ወይም ከጓደኞችሽ ጋር ምን ትሠሪያለሽ ?
ኢየሩስ፡-ለብቻዬ ምንም አልሠራም ከጓደኞቼ ጋር ኸርዋኸርዌ ፣ ገመድ ዝላይ ድብብቆሽ ሰኞና ማክሰኞ ኳስ እጫወታለሁ በማለት ኢየሩሳሌም ለጠየቅናት ጥያቄ መልስ ሰጥታናለች ።

አዘጋጂ
ወ ት ንብረት አበበ



## ወጣቶች.........

ከገጽ ፳፱ የዞረ

ተረካቢ መሆናቸውንም በተግባር በማሳየት ላይ ይገኛሉ ።

ስለሆነም በሲዳሞ ክፍለ ሀገር ወጣት መንፈሳዊያን ማኅበራት አጠቃላይ ማህበር አስተባባሪነትና ሰብሳቢነት በተለያዩ ቦታዎች በተወሰኑ ወራት እየተገናኙ መንፈሳዊ ሴሚናር ማካሄድ የተዋሕዶ እምነትን ትክክለኛ ተልዕኮ ለማወቅ ፍቱን መፍትሔ ነው በይበልጥም ለመቀራረብና ለመተዋወቅ ዓይነተኛ ምክንያት ይሆናል ለዚህም መንፈሳዊ ተልዕኮ የሰበካ ጉባኤያት የሚያደርጉት የገንዘብም ሆነ የሞራል አስተዋፅዖ በቀላሉ የሚታለፍ አይደለም ።

ይህም ሆኖ በቅዱስ ያሬድ ዜማ የተቀነባበሩ መዝሙሮችን ታላላቅ የሃይማኖት መሪዎች በሃይማኖታቸው ከአላውያንና ከአረማውያን ጋር ተከራክረው ያሸነፉባቸው ታሪካዊ ዓምዶችን በጠቅላላውም መንፈሳዊ መዘክሮችን አውቆ ማሳወቅ እንደተቀዳሚ ተግባር የሚመለከቱት ወጣቶች አንድነታቸውን በይበልጥ በማጠናከር ላይ ይገኛሉ ።

አበይት የቤተክርስቲያናት በዓላትን የወጣት መንፈሳዊያን ዓመታዊ መታሰቢያ ቀኖችን በህብረት በማክበር አስደሳች መልዕክቶችንና ወቅታዊ ተግባሮችን በማሳየት ላይም ናቸው ።

ይኸውም የመጀመሪያ ጊዜ ባይሆንም ግንቦት 3 ቀን 1972 ዓ.ም የሻሸመኔ ቅዱስ ሚካኤል መንፈሳዊያን ወጣቶች በተጠቀሰው ቀን ዓመታዊ በዓላቸውን እንደሚያከብሩ ለየማኅበራቱ ባስተላለፉት ጥሪ መሠረት በዕለቱ የተገኙት የየማህበራቱ ወጣት መዘምራንና አባላት ቁጥር ከአካባቢው ምእመናን ቁጥር ያላነሰ ነበር ።

ይህም በተመልካችነት ብቻ ሳይሆን ለእያንዳንዱ ማህበር በተሰጠው ፕሮግራም መሠረት መዝሙሮችንና ትምህር

ወደ ገጽ ፳፱ ዞሯል

www.ethiopianorthodox.org

# የመጽሐፍ ቅዱስ ጥያቄዎች

## ውድድር መልስ

ባለፈው ወር የትንሣኤ መጽሔት ላይ ከኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር የቀረቡ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥያቄዎች ውድድር ማቅረባችን ይታወሳል ። ለውድድሩ በርከት ያሉ ሰዎች ተካፋይ የሆኑ ሲሆን ፤ አሸናፊ ለሆናችሁ "እንኳን ደስ ያላችሁ!" እያልን ሽልማታችሁን በአድራሻችሁ መሠረት የላክን መሆኑን እንገልጻለን ።

መልስ፡-

1. ዮሴፍ በሕልሙ ሲሰግዱለት የተመለከተው፡- ፀሐይ ፣ ጨረቃና አስራ አንድ ከዋክብት ነበር ። (ዘፍ. 37፡9 )
2. ንጉሥ አርጤክስስን ከታቀደበት ሴራ ያዳነው ፡- መርዶክዮስ ይባላል ። -መ.አስ.6፡2)
3. አራት ታላላቅ አራዊት በሕልሙ የተመለከተ ነቢይ፡- ዳንኤል ነው ። (ዳን.7፡)
4. በምድረ እስራኤል ዝናም እንዳይጥል ያገደ ነቢይ፡- ኤልያስ ነበር። (1ኛ ነገ. 17፡1)
5. ያዕቆብ የእግዚአብሔርን ቃል፡- በመስተዋት ይመስለዋል ።(ያዕ 1፡2)
6. በያዕቆብ መልእክት መሠረት ክርስቲያን መከራ ሲገጥመው ፤ በትዕግሥትና በደስታ መቀበል አለበት ። (ያዕ. 1፡3)
7. በያቆብ አገላለጽ ንጹህና ነውር የሌለበት አምልኮ፡- ወላጆች የሌላቸውን ልጆችና ባልቴቶችን በመከራቸው መርዳት ፣ ከዓለምም

   ዕድፍ ሕይወትን መጠበቅ ።(ያዕ 1፡27)
8. በጉደለ የተሞሉ ቃላት ፤
   - ሀ. አጥብቀህ ልብህን ጠብቅ ፣ የሕይወት መውጫ ከእርሱ ነውና ። (ምሳ. 4፡23)
   - ለ. ልብሴን እርስ በርሳቸው ተከፋፈሉ ። (ዮሐ. 19፡24)
   - ሐ. ኑና እንዋቀስ ይላል እግዚአብሔር ። -ኢሳ. 1፡18)
   - መ. ልጆቼ ሆይ ኃጢአትን እንዳታደርጉ ይህን እጽፍላችኋለሁ ።(1 ዮሐ. 2፡₌)
   - ሰ. አምላክ ሆይ እኔን ኃጢአተኛውን ማረኝ ። (ሉቃ. 18፡13)

**የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር**

የፖ. ሣ. ቁጥር 1252
ስልክ 15 82 33
አዲስ አበባ

የፖ. ሣ. ቁጥር 700
ስልክ 113455 –
አሥመራ

## ወጣቶች.......

ከገጽ ፳፫ የዞረ

ታዊ መልዕክቶችን የማቅረብ ሁኔታም ስለነበር በዚህ መልካም ኢጋጣሚ እያንዳንዱ ዝግጅቱን አቅርቦአል ።

በበዓሉ ላይ የተገኙት ምእመናን በያንዳንዱ ማህበር በቀረቡት ዝግጅቶች የነበራቸውን ደስታ በእልልታ የገለፁ ሲሆን አጠቃላይ ገጽታው እጅግ የሚያስደስት ነበር ።

ሆኖም የወጣት መንፈሳዊያን በክፍለ ሀገር ሳይወሰኑ በቦታ ርቀት ሳይበገሩ የሚያደርጉት ክርስቲያናዊ መልእክት እጅግ የሚያስደስት ከመሆኑም በላይ ለወደፊቱ ለቤተክርስቲያናችን

ሕልውና አስተማማኝና ዘለቄታዊ ያለው ኃይል መሆናቸውን መተንበይ ስለማያዳግት ለክርስቲያኖች ሁሉ መልካም ዜና ነው ።

የወጣት መንፈሳዊያን ማህበራት በጣም በሚያስደስት ሁኔታ ላይ ያሉ በመሆኑና ለሌሎችም ማህበራት ጥሩ ምሳሌነት ያለው እንደመሆኑ መጠን በዚሁ እንዲቀጥል ልባዊ ምኞቴን እገልጣለሁ ።

ወንድሙ አየነው



# ኢ.ኦ.ተ.ሐ.ደ

ማሳሰቢያ ለምእመናን በሙሉ

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፣ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቅዳሴዎችን ፣ መንፈሳዊ ዘሙናዊ መዝሙሮችን ፣ ትምህርቶችንና የልማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየተከታተለ በቴፕ እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅርስ ያስቀምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የካሴት ክር ላቀረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ በማስከፈል ይሰጣል ።

ለዚሁ ጥያቄ ቢኖርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመረዳት ይቻላል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሐዋርያዊ ድርጅት
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት

ስልክ ቍ. 116616
የመል. ሣ. ቍ. 3137
አዲስ አበባ

www.ethiopianorthodox.org